የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ባህል፣ ቱሪዝም እና ፓርኮች ልማት ቢሮ
ባሕር ዳር

Amhara National Regional State
Culture, Tourism & Parks Development Bureau
Bahir Dar

ቁጥር ባቱ/ፖ/ኤ.ኤ/147
Date
ቀን 07/02/2007

ለሰሜን ጎንደር ኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ ተፈጥሮ ሀብት ፕሮግራም
ለሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ

ጎንደር፣
ለማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም
ማ/ሥላሴ፣
ለ3ቱ አዋሳኝ ወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች
ባሉበት፣

ጉዳዩ፡- የማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማጎበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ጥናት ሪፖርትን ይመለከታል

የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያላቸውን ቦታዎች በመለየት በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠበቅ እንዲቻል ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በማጥናትና በመከለል ህጋዊ ዕውቅና የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል።

በዚህም መሰረት በሰሜን ጎንደር ዞን ከሚገኙትና የተሻለ የደን ሽፋን ከለባቸው ቦታዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ወደ ተሻለና ዘላቂ የጥበቃ ስርዓት ለማምጣት ቢሯችን ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ በ2006 በጀት ዓመት ከሰሜን ጎንደር ዞን ኑሮ ማሻሻልና ዘላቂ ተፈጥሮ ሀብት ፕሮግራም ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የቢሮውን ባለሙያዎችን ወደ ቦታው በመላክ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ወሰን፣ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚገኙ የብዝሐ ሕይዎት ሃብቶች፣ በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ የሚገኙ ሰው ሰራሽ ችግሮችና ስጋቶች፣ የአካባቢውን መሰረታዊ የማጎበረ ኢኮኖሚ መረጃዎች እና የተፈጥሮ ሃብቱ በዘላቂነት የሚለማበትንና የሚጠበቅበትን የጥበቃ ስርዓት የሚያሳይ የዝርዝር ጥናት እንዲያካሂዱ አድርጓል።

በመሆኑም ቦታው ካለው ስነምህዳራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማጎበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ቢሮው በቀጣይ ዘላቂ የጥበቃ ስርዓት እስኪዘረጋለት ድረስ የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸውን ማከናወን ይችሉ ዘንድ 84 ገጽ የያዘውን የዝርዝር ጥናት ሪፖርት የላክን ሲሆን ለአጋር አካላት በማሳወቅ በሰነዱ ላይ ያላችሁን አስተያየት እስከ ጥቅምት 30/2007 ዓ.ም እንድትልኩልን እንጠይቀለን።

ከሰላምታ ጋር

D/All files/ letter header&footer MA
ፖ.ሣ.ቁ 1317, 1616
ስልክ 058-2-22-10-50
058-2-20-45-91
ፋክስ 058-2-22-18-34
058-2-20-26-50
ባህር ዳር

በጠንካራ አመራር ኤድስን አንግታ
መልስ በሚፅፉልን ጊዜ እባክዎን የኛን ደብዳቤ
ቀንና ቁጥሩ ይጥቀሱ
Please Quote our RefNº When Replaying
E-mail amhtour@ethionet.et
Website WWW.amharatours.org.et/tourism

P.O.Box1317, 1616
Tel.No 058-2-22-10-50
058-2-20-11-33
Fax 058-2-22-18-34
058-2-20-26-50
Bahir Dar

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ



በሰ/ጎንደር አስተዳደር ዞን የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ዝርዝር ጥናት ሪፖርት

የዱር እንስሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም
ዋና የስራ ሂደት







መስከረም/2007 ዓ.ም
ባህር ዳር

LISRMP-NG


አዘጋጆች፦
1. አበባው አባይነህ
2. አበጀዘውዴ
3.ብርሃነመስቀልዓለሙ
4.መኩሪያ አዲስ

ምስጋና

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን በገዳሙ አባቶች አርቆ አሳቢነትና አስተዋይነት ተጠብቆ ባይቆይ ኑሮ አሁን ላለው ትውልድ እንደ ሌሎቹ አካባቢዎች የተራቆተና የተጋጋጠ ቦታ በጠበቀው ነበር፡፡ የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም አባቶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ በተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ ዙሪያ ከመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት ግንዛቤ እየፈጠሩ ሃብቱ እንዲጠበቅ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣታቸው ባሻገር ይህን ጥናት አከናውነን በዘላቂነት የሚለማበትንና የሚጠበቅበትን ስልት ለመንደፍ ያለእነርሱ ሙሉ ፈቃደኝነት የሚሞከር አልነበረም፡፡ ከዚህም ባለፈ ጥናቱንና ክለላውን ስናከናውን ጥሩ የሆነ አቀባበል ከማድረግ ጀምሮ ለስራው አስፈላጊውን ሰው መድበው ፣ በጸሎታቸውና በሀሳባቸው ደግፈውና ሙሉ መስተንግዶ አድርገውልናል፡፡ ለዚህም ባናመሰግናቸው በበረሃ ተሰደው ከጣዕመ ዓለም ርቀው የሚያመልኩት አምላካቸው ይታዘበናል፡፡

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን የዳሰሳና የዝርዝር ጥናት ለማካሄድ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የተባበረንን የሰሜን ጎንደር ኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮግራምን ክልብ ልናመሰግን እንወዳለን፡፡ የሰሜን ጎንደር ኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮግራም ምንም እንኳን የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደንን በ2006 ዓ.ም ለማጥናት የበጀትም ሆነ የስራ ዕቅድ ባይዝም እኛ ያቀረብንለትን የበጀት ድጋፍ በቀናነት ፈጣን የሆነ ምላሹን ባይሰጠን ኑሮ ስራችን ከዚህ መድረስ ባልቻለም ነበር፡፡ የሰሜን ጎንደር ኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮግራም ከበጀት ድጋፉ በተጨማሪ በ2001 ዓ.ም የገዳሙን የተፈጥሮ ደን ክልል ከሰሜን ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ ጋር በመቀናጀት ኃላፊነቱን ወስዶ ዳር ድንበሩ በመለየቱ አሁን ያለውን የደን ክልል ስፋት እንድናገኝ አስችሎናል፡፡ ፕሮግራሙ የገዳሙን አባቶች ከጎናቸው ሆኖ ባያግዛቸውና ዳር ድንበሩን ለይተው መጠበቅ ባይችሉ ኖሮ ከተለያዩ አካላት በሚደርሰው ጫና አሁን ያለውን 19070 ሄ/ር የተፈጥሮ ደን ክልል ማግኘት ቀርቶ የዚህን ሩቡን እንኳን ለማግኘት አጠራጣሪ ነው፡፡

ስራችን ዳር እንዲደርስ የበረሃውን ሀሩር፣ ረሀቡንና ጥሙን ታግሰው አቀበቱንና ቁልቁለቱን በመውጣትና በመውረድ አብረውን ለደከሙት የመተማ ወረዳ ልዩ ልዩ ጽ/ቤቶች ባለሙያዎች እና ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው የመስክ መረጃችንን በማድመጥ በቀጣይ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኝነታቸውን በማረጋገጥ ሞራላችንን ለገነቡት የሦስቱ ወረዳ(መተማ፣ ቋራና ጭልጋ) አመራሮች ከፍተኛ አክብሮት አለን፡፡

ማውጫ **ገጽ**

ምስጋና iii

1. መግቢያ 1

1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት 2

1.3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ 3

1.3.1 መገኛና ስፋት 3

1.3.2 የአየር ንብረት 4

1.3.3 የመሬት አቀማመጥና የአፈር አይነት 5

1.4. የጥናቱ ዓላማ 5

1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ 5

1.5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች 6

1.5.1 የጥናቱ ስልቶች 6

1.5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች 7

1.5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 7

2. የጥናቱ ውጤት 8

2.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ 8

2.2 የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ 9

2.3 የዱር እንስሳት 11

2.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት 13

2.5 የውሃ ሀብት፡- 14

2.6 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና አካባቢ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ 17

2.6.1 የገዳሙ የገቢ ምንጮች 17

2.6.2 የመናኝ አባቶች የስራ ክፍፍልና የስራ ባህል 19

2.6.3 የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች ሶሽዮ ኢኮኖሚ 22

2.7 የቱሪዝም አቅም ጥናት 29

2.7.1.የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም 29

2.7.2. በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ዙሪያ የሚገኙና በባህርዳር፣ ጎንደር፣ መተማ የቱሪስት መንገድ ላይ መስብኘት የሚችሉ ዋና ዋና የባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ ሃብቶች 35

2.8. በታሣቢ ጥብቅ ሥፍራው በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ የሚታዩ ተጽዕኖዎች /ስጋቶች/ 42

3. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ 45

4. ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች 47

5. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና 50
6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 54
7. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች 54
8. የጉዳዩ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና 56
8.ዋቢ መጽሐፍት (References) 63
እዝል1. በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በጥናት ወቅት የተለዩ ዕፅዋት 66
እዝል2. በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በጥናት ወቅት የተለዩ የዱር እንስሳት 68
እዝል3. በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በጥናት ወቅት የተለዩ አዕዋፍት 70
እዝል4. በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የዳር ድንበር ኮርድኔት 72
ዕዝል 5 በማኅበረ ሥላሴና አካባቢው ጠቃሚ የሆኑ ዋና ዋና የጂፒኤስ ነጥቦች/ንባቦች 79

1. መግቢያ

በአሁኑ ወቅት ብዝሀ ህይወት ከመደበኛው የዝርያዎች የመለወጥና የመጥፋት ሂደት ከ1000 እጥፍ በላይ የፈጠነ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ከእነዚህ የጥፋት ምክንያቶች ዋነኛው የሰው ልጆች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመሩ የተነሳ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ምችጌዎችን በማውደማቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በመሆኑም ጥብቅ ሥፍራዎች ምቹጌንና ብዝሀ ህይዎትን በመጠበቅ ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም እንዲጎለብት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ በዚህ ክፍለ ዘመን ጥብቅ ስፍራዎችና የብዝሀ ህይወት ለምዕተ አመቱ የልማት ግቦች መሳካት ዋና መሰረቶች መሆናቸውንና እነሱን በአግባቡ መጠበቅና መጠቀም ካልቻልን ልናሳካቸው እንደማንችል የአለም ማህበረሰብ የተረዳበትና ዘላቂነት ያለው የሀብት አጠቃቀም ማስፈን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን የተገነዘቡበት ወቅት ነው፡፡

የሰው ልጅ ስለብዝሀ ህይወት ጠቀሜታ የአሁኑን ያክል ባልተገነዘበበት ወቅት በክልሉ የሚገኙ በርካታ የተፈጥሮ አካባቢዎች ለረጅም ዓመታት በሰው ልጆች ተፅዕኖ ውስጥ ወድቀው ቆይተዋል፡፡ አንዳንድ አካባቢዎች እንዲያውም ከመሸከም አቅማቸው በላይ (beyond the amount of disturbance that ecosystems can tolerate) አገልግሎት እንዲሰጡ በመደረጋቸውና በመውደማቸው ሰዎች አካባቢያቸውን ለቅቀው እንዲሰዱ እየተገደዱ ይገኛሉ፡፡ በደጋማውና በወይናደጋማው የክልላችን ክፍል በተከሰተው ከፍተኛ የስነምህዳር መዛባት የተነሳ ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ባለማግኘታቸው ከአካባቢያቸው ተሰድደው በዚሁ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ ወረዳዎች እየሰፈሩ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ መሬቱና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የተፈጥሮ ሐብቶች በከፍተኛ ሁኔታ አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን አጠቃቀማቸው ግን የእለት ጥቅምን ብቻ መሰረት ያደረገ በመሆኑ በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በክልሉ 5 ብሄራዊ ፓርኮች እና አንድ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ያሉ ሲሆን ይህም በIUCN መስፈርት መሰረት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት 10 ከመቶ መሸፈን ያለበት ቢሆንም እነዚህ ጥብቅ ስፍራዎች ከጠቅላላ የክልሉ ቆዳ ስፋት የሚሸፍኑት 2.5 ከመቶ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከአሁን በፊት የጥናት ስራቸው የተጠናቀቁት የወፍ ዋሻ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ፣የወለቃ አባይና በቶ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ፣የጉና ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ፣የአቡነ የሴፍ፣አቦይ ጋራና ዝጊት ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራና አሁን የጥናት ሰነዱ የተዘጋጀለት የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ህጋዊ እወቅና ማግኘት ቢችሉ የክልሉን የጥብቅ ስፍራ ሽፋን ወደ 3.011 ከመቶ ከፍ ያደርገዋል፡፡

ቢሮው በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት አንዱ በክልሉ ውስጥ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ያላቸውን ቦታዎች በማጥናትና በመከለል ህጋዊ እውቅና እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን መተማ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባበውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር ጥናት ተከናውኗል፡፡ የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በዋናነትየ Sudan–Guinea Savanna ባዮም እና *Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን የስርዓተ-ምህዳሩ መገለጫ የሆኑትን እንደ የአባሎ ዝርያዎች ፣ዛና ፣ሽመል፣ክርክራ ፣ዋልያ መቀር የመሳሰሉትን የዕዕዋት ዝርያዎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህ ስርዓተ ምህዳር በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክ ፣በባጉሳ ብሄራዊ ፓርክ እንዲሁም በአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በከፊል የተወከለ ሲሆን የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ወደ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ማደግ የበረሃማነት መስፋፋትን እንደመቀነት በመሆን እየተከላከለ ያለውን የአባሎ-ወይባን /*Combretum-Terminalia* Woodland/ ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ያሰፈዋል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ 861 የወፍ ዝርያዎች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ 668 የወፍ ዝርያዎች የሚገኙ ሲሆን በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም እና አካባቢው በጥናቱ ወቅት ከ96 በላይ ዝርያዎች ተለይቷል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ በSudan–Guinea Savanna biome ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍ ዝርያዎች ውስጥ ደረተ ቀይ ንበበል /Red-throated bee-eater / በገዳሙ ውስጥና በአካባቢው ተጠልላ እንደምትኖር ተረጋግጧል፡፡ በሀገራችን ከሚገኙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት ከተቃረቡ (Globally threatened) 31 ዝርያዎች ውስጥ 21 በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ባለ ነጭ ጀርባ የአፍሪካ ጥንባንሳ /African white backed Vulture (EN) ፣Red-footed Falcon (NT) እና ባለነጭ ራስ ጥንባንሳ /White headed vulture (VU) በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የብዝሃ ህይዎት አመላካች የሆኑትን የወፍ ዝርያዎች አቅፎ የያዘ መሆኑ የተረጋገጠበት ነው፡፡

1.2. የጥናቱ አስፈላጊነት

- በክልሉ ያሉ የጥብቅ ስፍራዎችን ቁጥር በመጨመር በክልሉ የሚገኘውን ወካይ የተፈጥሮ ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ማሳደግ በማስፈለጉ፣


- የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር (Sudano-Guinean biome) በእርሻ መስፋፋት፣ ህገ ወጥ አደን፣ ሰፈራ እና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ችግር እየደረሰበት ያለ በመሆኑ የችግሩን መነሻና መፍትሄ ለማፈላለግ ጥናት ማድረግ በማስፈለጉ፣
- በውስጡ የሚገኘውን የብዝሃ ህይወት ሃብት አቅም ማወቅ በማስፈለጉ፣
- የተፈጥሮ ደኑን አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና የቱሪዝም ጠቀሜታና አቅም ማወቅ በማስፈለጉ፣
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ህጋዊ እውቀና ለማሰጠት የክለላ ስራው በአግባቡ የተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣

1.3. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ አጠቃላይ ሁኔታ

1.3.1 መገኛና ስፋት

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን በዋናነት በመተማ ወረዳ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ጭልጋና ቋራ ወረዳዎችም ያዋስኑታል። ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በሶስት ወረዳዎች ውስጥ ከሚገኙ አምስት ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰን ነው። ጠቅላላ ስፋቱም ከ19070 ሄ/ር በላይ እንደሚደርስ የክለላ ጥናቱ ውጤት ያመለክታል። አካባቢው በሰሜን ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በዚህ የልማት ቀጠና እና በእንዲህ አይነት ስነምህዳር ከአሁን በፊት የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ባለመቋቋሙ በቀጠናው ወሳይ ሊሆን ይችላል።

የማኅበረ ስላሴ አድነት ገዳም የሚገኘው ከጎንደር ወደ መተማ በሚወስደው የአስፓልት መንገድ 132 ኪ.ሜ. ላይ ደረቅ አባይ ቀበሌ ሲደርሱ ወደ ደቡብ በመታጠፍ ያለውን ጊዜያዊ መንገድ በእግር ከሆነ አራት (4፡00) ስዓት፤ በመኪና ከሆነ ደግሞ 40 ደቂቃ ከተጓዙ በኋላ ግዝት በር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ ይደረሳል። እንዲሁም የመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው የገንዳውሃ ከተማ ከተነሱ ወደ ጎንደር ከተማ በሚወስደው የአስፓልት መንገድ 27 ኪ.ሜ. ላይ ደረቅ አባይ ቀበሌ ሲደርሱ ወደ ደቡብ በመታጠፍ ያለውን ጊዜያዊ መንገድ በመያዝ በተመሳሳይ መጓዝ ይቻላል።



ምስል1. *የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም መሰረታዊ ካርታ*

አካባቢው በ$12^0 25' 35.77''$ እስከ $12^0 34' 51.93''$ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ$36^0 25' 38.32''$ እስከ በ$36^0 37' 387.30''$ ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታም ከ641 እስከ 1362 ሜትር ይደርሳል፡፡ የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አካባቢ በስተምስራቅ በጭልጋ ወረዳ ከሚገኘው ሽኃርዳ ቀበሌ ፤በስተሰሜን በመተማ ወረዳ ከሚገኙት ከሌንጫና አኩሻራ ቀበሌዎች ፤በምዕራብ በቋራ ወረዳ ውስጥ ከሚገኘው ኮዝራና በመተማ ወረዳ ከሚገኘው ሻሸጌ ቀበሌዎች እንዲሁም በስተደቡብ ከሻሸጌ ቀበሌ ይዋሰናል፡፡

1.3.2 የአየር ንብረት

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አካባቢ ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምን በስርዓተ ምህዳር ደረጃም የአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ-ምህዳርን ይወክላል፡፡

በአካባቢው የሜትሮሎጂ ጣቢያ ባለመኖሩ በትክክል የተወሰደ የዝናብና የሙቀት መጠን መረጃ ባይኖርም ከአካባቢው የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመተማ ወረዳ የዝናብ መጠን ከ665-1132ሚ.ሜ እንዲሁም አማካይ የዝናብ መጠን 955 ሚ.ሜ እንደሚደርስና የወረዳው አማካይ ከፍተኛና ዝቅተኛ የሙቀት መጠን 36 እና 19^oc እንደሚደርስ መረጃዎች ያሰረዳሉ (Abeje Eshete,2005)፡፡ የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አመታዊ የዝናብ መጠን ምንም እንኳን ከቦታው የዝናብ መጠን መመዝገቢያ ባይኖርም ከተወሰዱ የዲጂታል መረጃዎች 957 ሚ.ሜ ይደርሳል፡፡

(http://www.samsamwater.com/climate/climatedata.php?lat=12.5107&lng=36.60878&loc=Amhara+%2CEthiopia)

1.3.3 የመሬት አቀማመጥና የአፈር አይነት

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አካባቢ የመሬት አቀማመጥ 20.68 ከመቶ ሜዳማ፣ 50.01 ከመቶ ተዳፋታምና 25.31 ከመቶ ገደላማ እንደሆነ ከባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የGIS ክፍል የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ ።።


የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የአፈር አይነትን ስንመለከት ከአብክመ ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የGIS ክፍል የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሰረዱት

Orthic solonchaks 21.21%

Eutric nitisols 36.29%

Chromic cambisols 23.29%

Orthic luvisols 19.21% የተሸፈነ ነው።።



ምስል 2. የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የመሬት አቀማመጥ ካርታ

1.4. የጥናቱ ዓላማ

በሰሜን ጎንደር ዞን መተማ ወረዳ ውስጥ በሚገኘው የማህበር ስላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ህይወታዊ፣ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የመስህብ ሃብቶች ላይ ዝርዝር ጥናት በማካሄድ የአካባቢውን ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ማደራጀትና መተንተን ነው፣

1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ጥበቃ ህብረት /IUCN/ መስፈርት መሰረት

- የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ውስጥ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና እጽዋት ዝርያና የዝርያ ክምችት እንዲሁም የተፈጥሮ ገጽታ ይዘት ዝርዝር ጥናት ማካሄድ፣
- በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ውስጥና በአካባቢው የሚገኙ የመስህ ሃብቶችን በመለየት ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸውን አቅም ማጥናት፣

- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና አካባቢ ያለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በማጥናት ከታሳቢ ጥብቅ ሰፍራው ጋር ያላቸውን ቁርኝት መለየት
- የታሳቢ ጥብቅ ቦታው መቋቋም ለሀገራዊና አካባቢያዊ ልማት የሚኖረውን ሚና በዝርዝር ማጥናት፣
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው አጋር አካላት ሊኖራቸው የሚችለውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት ወደፊት አካባቢው ወደ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፋራነት ሊመጣ የሚችልበትን ሁኔታ ማመላከት፣

- በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የተከናወነው የዳር ድንበር ክለላ በጥብቅ ስፍራ የክለላ መስፈርት መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.5. የጥናቱ ስልቶችና ቁሳቁሶች

1.5.1 የጥናቱ ስልቶች

የማህበረ ስላሴን አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ጥብቅ ስፈራ የመሆን አቅም ለመወሰን የተጠቀምንበት የጥናት ስልት ገላጭ የሚባለው የጥናት ስልት (descriptive survey) ሲሆን ስልቱን የመረጥንበት ምክንያት በተፈጥሮ አካባቢ ጥናቶችን ለማካሄድ፣ ሁነቶችን ለመግለጽ፣ ለማወዳደርና በሚሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት የማጠቃለያ ሀሳቦችን ለማደማደም ስለሚያስችል ነው።።

ለዚህ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በመጠንና በአይነት የተሰበሰቡ ሲሆን የመጠን መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅና በመስክ ምልከታ፤ የአይነት በረጃዎች ደግሞ በቡድን ውይይት ፣ በቃለ መጠይቅና በመስክ በምልከታ ተሰብስበዋል።።

በጥናቱ ወቅት የሚመለከታቸውን አጋር አካላትን በመያዝ የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምንና የገዳሙን አካባቢ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ኢኮሲስተም ፣ የአካባቢው ብዝሃ ህይወት ሃብት ይዘትና የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል፣ ይህንም ጥናት ለማካሄድ የጥናት የጉዞ መስመሮችንና የተለያዩ የመስክ መሳሪያዎችን ተጠቅመናል።። ዕፅዋትን፣ ታላላቅ አጥቢዎችንና አዕዋፍን ለመለየት ጋይዶችን፣ባይኖኩላርና ድጂታል ካሜራዎችን ተጠቅመናል

ከዚህ በተጨማሪ ለጥናቱ የሚያግዙ የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ከኢንተርኔት እንዲሁም ከማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም፣ ከአዋሳኝ ወረዳዎችና ከሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን የተለያዩ ሴክተር መ/ቤቶች ተሰብስበው ጥቅም ላይ ውለዋል። ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች በማደራጀትና በመተንተን የጥናቱን ውጤትና ያሉ ዋና ዋና ችግሮችን የለየን ሲሆን እያንዳንዱ አጋር አካልም መስራት ያለበትን ለይተናል።

1.5.2 ለጥናቱ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶች

- ጂፒኤስ.....1
- ባይኖኩላር.....1
- ዲጂታል ፎቶ ካሜራ.....1
- ቶፖ ሸት..... (የአካባቢውን ቶፖሸቶች)
- ጋይድ ቡክ.....(የአእዋፍት፣ የአጥቢዎችና የዕፅዋት ማረጋገጫ መጽሐፍት)

1.5.3 የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

- ስለማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ተሰብስበዋል፣
- በማህበረስላሴ አንድነት ገዳምና በገዳሙ አካባቢ ያሉ ባህላዊና ተፈጥሮዊ ቅርሶች ተለይተዋል፣
- በማህበረስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳት፣ ዕፅዋት፣ ሥርዓተ-ምህዳርና የሶሽዮ-.ኢኮኖሚ ሃብቶች መረጃ ተሰብስቧል፣
- ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው ያለው አጠቃላይ መረጃ ተሰብስቧል ፣
- የቱሪስት መመልከቻ ሊሆኑ የሚችሉ ቦታዎች ተለይተዋል
- ከማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የሚነሱ ዋና ዋና ወንዞች ተለይተዋል
- በአካባቢው እየደረሱ ያሉ ዋና ዋና ተጽዕኖዎች ተለይተዋል

2. የጥናቱ ውጤት

2.1 ስለ ተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስልትና ታሪክ

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የተመሰረተው በ4ኛው ክፍለ-ዘመን በአብርሃ ወአጽብኃ ዘመነመንግስት በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን መሆኑንና በወቅቱ ማለትም ገዳሙ በተመሰረተበት ወቅት አካባቢው በሰው ልጆች ተጽዕኖ ያልወደቀና ወደ አካባቢው መድረስ አስቸጋሪ እንደነበር ከገዳሙ የተገኙ መረጀዎች ያስረዳሉ፡፡ የአካባቢው ተፈጥሮ ሃብትና የጥበቃ ስራ በገዳሙ መተዳደር የጀመረው በዚሁ ጊዜ ነው፡፡ ገዳሙ ከ1624 ዓ.ም በፊት 44 ጉልት ያሰተዳድር እንደነበርና ከአፄ ፋሲል ንግስና በኋላ ከደንገል በር እስከ ድንድር ድረስ ያለውን ቦታ ገዳሙ እንዲያሰተዳድር ተሰጥቶት በአካባቢው ያለውን የተፈጥሮ ሃብት ጨምሮ ሲሰተዳድር መቆየቱን መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

ገዳሙ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በአካባቢው ግብር ሲያሰገብር፣ ወንጀልን ሲከላከልና በአከባቢው ከደጋ የሚመጡ ነዋሪዎችንም ሲያሰፍር ቆይቷል /ለምሳሌ የሌንጫ ቀበሌ ነዋሪዎችን/፡፡ እንዲሁም ገዳሙ ወደበርዜን የሚባል የጉምሩክ ኬላ እንደነበረውና እያስገበረ አንድ እጅ ለገዳሙ ሁለት እጅ ደግሞ በጊዜው ለነበረው የሀገሪቱ መንግስት ያስገባ ነበር፡፡ አንዲህ አያለ አስከ 1966 ድረስ አካባቢውን ሲያሰተዳድር የቆየ ቢሆንም ከዚያ ወዲህ የራሱን ክልል ብቻ በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ የገዳሙ ክልል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አጋዘን ተራራ ድርስ ይደርስ እንደነበረ የገዳሙ መነኮሳት ይናገራሉ፡፡ በ1977 ዓ.ም በገዳሙ ፈቃድ እንቡልቡል አካባቢ ስምንት አባወራዎች በጉልበታቸው ገዳሙን እያገለገሉ ሰፈረው እንዲኖሩ ገዳሙ የፈቀደላቸው ሲሆን በሂደት ከ70 አባውራ በላይ የደረሱ በመሆኑ ይህም ለተፈጥሮ ሃብቱ ውድመት መንስዔ በመሆኑ በ2001 በተደረገው የገዳሙን ክልል የመለየት ስራ ከገደሙ ክልል እንዲዎጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስምምነት ላይ በመደረሱ በ2003 ዓ.ም ከገዳሙ ክልል እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

በአዋሳኝ ቀበሌዎች ያለው የተፈጥሮ ሀብት በከፍተኛ ፍጥነት እየጠፋና እየተሟጠጠ በመሆኑና ማህበረሰቡ ሀብቱን ለመጠቃም ያላቸው ዝንባሌ ከፍተኛ በመሆኑ ብዝሀ ህይዎቱ በመጥፋት አፋፍ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ወዲህ ከጭልጋና ጣቁሳ አካባቢ በሚመጡ ህገወጥ ሰፋሪዎች በቦታው ላይ ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን

የገዳሙ ዙሪያም በእርሻ ተከቦ ይገኛል፡፡ የጥበቃ ስራውን ገዳሙ እስከ 2001 ዓም ከገዳሙ ገንዘብ በመመደብ ሲያስጠብቅ ከቆየ ቢሆንም በሀብቱ ላይ የሚደርሰው ውጫዊ ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱና ከገዳሙ አቅም በላይ በመሆኑ የመተማ ወረዳ አስተዳደር መንግስታዊ ተቋማት ከሰሜን ጎንደር ኑሮ ማሻሻልና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮገራምና ከአማራ መልሶ ማቋቋምና ልማት ድርጀት ጋር በመሆን የጥበቃ ጥረቱን ሲደግፉ ቆይተዋል ፡፡ ሆኖም ግን የተሰማሩት የጥበቃ ሰራተኛ ቁጥር በቂ ባለመሆኑና የብዝሀ ህይወት የጥበቃ ስልት ስልጠና ያልተሰጣቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም በአካባቢው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህገወጥ መንገድ መሬቱን፣ እጽዋቱንና የዱር እንስሳቱን የመጠቀም ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በአሁኑ ጊዜ በገዳሙ የብዝሀ ህይወት ሀብት ላይ ከፍተኛ ጫና እየደረሰበት ይገኛል፡፡

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ሃይማኖታዊ ስርዓትን ከመፈጸም በተጨማሪ ደንን በመጠበቅና ለአካባቢ ጥበቃ እያደረገ ላለው አስተዋፅዖ የብሄራዊ አረንጓዴ ሽልማት ፕሮግራም 2001 የሲቪል ማህበረሰብ ምድብ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ በመሆን ዋንጫና የምስክር ወረቀት ከቀድሞው ፕሬዘዳንት ክቡር ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ እጅ ሽልማት አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አረንጓዴ ሽልማት ፕሮግራም 2001 የሲቪል ማህበረሰብ ምድብ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ በመሆን ዋንጫና የምስክር ወረቀት ተሸልመዋል፡፡



ምስል 3. *የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የአረንጓዴ ሽልማት የምስክር ወረቀት*

2.2 **የስርዓተ ምህዳር ሁኔታ**

የማህበረስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የ Sudan–Guinea Savanna **ባዮም እና** *Combretum-Terminalia* Woodland **ስርዓተ ምህዳርን የሚወክል ሲሆን የዚህ ስርዓተ ምህዳር መገለጫ የሆኑትን የአባሎ ዝርያዎች** (*Combretum molle ,Combretum aculeatum, Combretum adenogonium, Combretum collinum)* **የወይባ ዝርያዎች** (*Terminalia laxiflora and Terminalia macropetra)*



ምስል 4. የማንበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ስርዓተ ምህዳር

- **ዋልያ መቀር** (*Boswellia papyrifera*)
- **ሽመል** (*Oxytenanthera abyssinica)*
- **ክርክራ** (*Anogeissus leiocarpa*)
- **ዛና** (*Stereospermum kunthianum*)
- *Lannea* spp (*Lannea chimperi and Lannea coromandelica*) **አቅፎ የያዘ ነው :: ይህ ስርዓተ ምህዳር በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክ ፣በባኑሳ ብሄራዊ ፓርክ እንዲሁም በአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በከፊል የተወከለ ሲሆን የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ወደ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ማደግ የበረሃማነት መስፋፋትን እንደመቀነት በመሆን እየተከላከለ ያለውን የአባሎ-ወይባን** /*Combretum-Terminalia* Woodland **ስርዓተ ምህዳር የጥበቃ ሽፋን ያሰፈዋል፡፡**

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምን አቅፎ በያዛቸው ዋና ዋና ዕጽዋት ሽፋን በሰባት ከፍሎ ማየት ይቻላል

- **በሽመል የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በአካባቢው ለመጥፋት አደጋ የተጋረጠበትን ሽመል አቅፎ የያዘ ሲሆን በዋናነት በአርባጫ ተራራ፣ በግዝት ክልል ተዳፋታማ አካባቢና በጉርማስ ተራራ ምስራቃዊ አካባቢ በብዛት ይገኛል፡፡**
- **ወንዝን ተከትለው የበቀሉ ታላላቅ ዛፎች የተሸፈነ ይህ የሽፋን አይነት በገዳሙ ውስጥና ድንበር በሚገኙ ወንዞች የማርያም ውሃ፣ሽመል ውሃ፣ ሰይጣን ባህር ፣ሆደጥርና ገንዳ ውሃ ወንዞችን ተከትሎ ዓመቱን በሙሉ አረንጓዴ የለበሱ ታላላቅ ዛፎችን እንደ ሰርኪን፣ዶቅማ ፣ደምበቃ ፤ክርክራ፣ኩመር እና ሌሎችንም ዛፎች አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህ አካባቢ በዋናነት ጉሬዛ በብዛት የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡**
- **በወንበላ የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በወንበላ ዛፍ የተሸፈነ ሲሆን ሌሎችንም አንደ ጫሪያ፣እንኩድኩዳ፣ዳርሌ ክርክርና ጭልቅልቃ የመሳሰሉ ዛፎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን የከርከመች፣የኩክቢና ጉርማስ አካባቢዎችን ያጠቃልላል፡፡**
- **በጓሪያ የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በጓሪያ የተሸፈነ ሲሆን ሌሎችን የግራር ዝርያዎችና የአርካ ዛፎችን አቅፎ የያዘ ሲሆን በሽመል ውሃ ሞፈር ቤትና በገንዳ ውሃ ወንዝ መሻገሪያ ያለውን አካባቢ ያጠቃልላል፡፡**

- በክርክራ የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በክርክራ ዛፍ የተሸፈነ ሲሆን ገርድም ሞፈር ቤት ፣ በሽመል ውሃ ሞፈር ቤትና በለምለም ተራራ ያለውን አካባቢ ያጠቃልላል፡፡
- በዋልያ መቀርና ዳርሌ የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በዋልያ መቀርና ዳርሌ ዛፎች ዛፍ የተሸፈነ ሲሆን በሌንጫ ቀበሌ አዋሳኝ፣በግዘት በርና በማርያም ውሃ ሞፍርቤት መካከል ያለውን ተዳፋታማ መሬት ያጠቃልላል፡፡
- በሲና የተሸፈነ ይህ አካባቢ በዋናነት በሲና ዛፍ የተሸፈነ ሲሆን በገዳሙ አናት ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ሌሎች የገዳሙ አካባቢዎች በተለያ የእጽዋት ዝርያዎች ተሸፍኖ ይገኛል፡፡

ይህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ለአካቢውና ለታችኛው ተፋሰስ በውሃ ምንጭነት የሚያገለግሉ ለገንዳ ውሃ ገባር የሆኑ እንደ ሽመል ውሃ፣ኩሻና ፈፋ ወንዞች እንዲሁም ለሸንፋ ወንዝ ገባሪ የሆኑ እንደ ማርያም ውኃ፣ ሰይጣን ባህርና ሆደ ጥር ወንዞችን አቅፎ የያዘ በመሆኑ ለታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳትም ሆነ ለአዕዋፍት የውሃ ችግር እንዳይኖር አስችሏል፡፡

2.3 **የዱር እንስሳት**

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ከአሁን በፊት ብዙ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ተጠልለው እንደቆዩበትና እንደ ዝሆንና አንበሳ የመሳሰሉ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ታሪካዊ የመኖሪያ አካባቢ እንደነበረ ከገዳሙ እጅ በንብረትነት የሚገኙ የዝሆን ጥርስ ቅሪትና የአንበሳ ጥፍር በመረጃነት መጥቀስ የሚቻል ሲሆን አንበሳ እስከ 1980ወቹ መጀመሪያ አካባቢ በገዳሙና አካባቢው እንደነበረ ከገዳሙ ያሉ አባቶች ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም ግን አካባቢው እየደረሰበት ባለው አሉታዊ ተጽዕኖ ምክንያት የዱር እንስሳት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ የዱር እንስሳትን በቀላሉ ማየት አዳጋች ሲሆን ጉሬዛ ግን በገዳሙ ውስጥ ባሉ ወንዞች አካባቢ በሚገኙ ታላላቅ ዛፎች ላይ እንደልብ የሚታይ ሲሆን ጉሬዛን ለማየት ለሚፈልጉ ጎብኝዎች ትክክለኛ ቦታው ይህ ነው፡፡



ምስል 5. *የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የዱር እንስሳት አመላካቾች*

አሁን ካሉት የዱር እንስሳት ውስጥ የጥበቃ ማዕከል ይሆናል ተብሎ የታሰበው ለቆላ አጋዘን ሲሆን አሁን በቦታው ላይ ከሚካሄደው ከፍተኛ አደን የተነሳ በግዘት በር አካባቢ ተወስኖ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከ26 በላይ አጥቢ የዱር እንስሳትና ከ96 በላይ አዕዋፋት፣ ዝርያዎች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚታወቁት

ከታላላቅ አጥቢ እንስሳት መካከል:-

- የቆላ አጋዘን (Greater kudu)
- ነብር (Leopard)
- ተራ ቀበሮ (Common/Golden Jackal)
- ድኩላ (Common bushbuck)
- ጉሬዛ (Abyssinian colobus)
- ሚዳቋ (Common duiker)
- ጅብ (Spotted Hyena)
- ዝንጅሮ (Anubis baboon)
- ቀይ ጦጣ (Patas monkey)
- አውጭ (Aardvark)
- ጦጣ (Vervet Monkey)
- የዱር ዓሳማ (Bushpig) ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ለዝርዝር መረጃ ዕዝል ሁለትን ይመልከቱ፡፡ በዕዝል ሁለት ከተመለከቱት ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት ውስጥ Aardvark (EN) እና Honey badger (VU) በIUCN የቀይ መዝገብ መጽሃፍ ሰፍረው የሚገኙ በመሆኑና ልዩ ትኩረት የሚሹ በመሆናቸው የዚህ ቦታ እውቅና መግኘት ዝርያዎችን መጠበቅ ያስችላል፡፡

አዕዋፋትን በተመለከተ በኢትዮጵያ ውስጥ 861 የወፍ ዝርያዎች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ 668 የወፍ ዝርያዎች የሚገኙ ሲሆን በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም እና አካባቢው በጥናቱ ወቅት ከ96 በላይ የወፍ ዝርያዎች ተለይቷል፡፡ የኢትዮጵያ የዱር እንስሳትና የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር (Ethiopian Wildlife and Natural History Society) እና በርድ ላይፍ ኢንተርናሽናል (Bird Life International) በዓለም አቀፍ ደረጃ በSudan–Guinea Savanna biome ክልል ውስጥ ከሚገኙ የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ

12 ያህሉ በሀገራችን እንደሚገኙና ከእነዚህ ውስጥ ደረተ ቀይ ንበበል /Red-throated bee-eater በገዳሙ ውስጥና በአካባቢው ተጠልላ እንደምትኖር ያሳያል። ከዚህ ሌላ በሀገራችን ከሚገኙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጥፋት የተቃረቡ (Globally threatened) 31 ዝርያዎች ውስጥ 21 በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ባለ ነጭ ጀርባ የአፍሪካ ጥንባንሳ /African white backed Vulture (EN) ፣Red-footed Falcon (NT) እና ባለነጭ ራስ ጥንባንሳ /White headed vulture (VU) በአካባቢው ተጠልለው እንደሚኖሩ በጥናቱ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን የተለያዩ በቀለማቸውና በዝማሬያቸው የሚማርኩ የአዕዋፍ ዝርያዎች መገኛ በመሆኑ በተለይም Red-billed Hornbill በአካባቢው በብዛት የሚገኝ በመሆኑ አካባቢው ለአዕዋፍ ጥበቃና ጉበኝት በጣም ወሳኝ ነው። በአካባቢው የሚገኙ የወፍ ዝርያዎችን ቁጥር በትክክል ለማዎቅ በተለያየ ወቅት ጥናት ማድረግ የሚያሰፈልግ ሲሆን በጥናቱ ወቅት የተገኙ የአዕዋፍ ዝርያዎችን ዕዝል ሶስት ላይ ይመልከቱ።

2.4 የዕፅዋት ሽፋንና ዓይነት

በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ከ100 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች በጥናት ወቅቱ የተመዘገበበት የተፈጥሮ አካባቢ ነው። ይህ አካባቢ በዋናነት *Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተምህዳር ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን እንደ ዋልያ መቀር፣ ዞቢ፣ ሰርኪን፣ ሲና፣ አባሎ፣ ደምበቃ፣ ባርካና፣ ካርማ፣ ሽመል፣ ክርክራ፣ ጫሪያ፣ ጓሪያና ሌሎችም ዕፅዋት የሚገኙበት አካባቢ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ 163 የእፅዋት ዝርያዎች ለመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው እና) በIUCN ቀይ መዝገብ ላይ የሰፈሩ (Kerry and Harriet, 1998) ሲሆን ከነዚህም ውስጥ

- ዲዛ *(Adansonia digitata)*
- ዞቢ *(Dalbergia melanoxylon)*
- ሰርኪን *(Diospyros mespiliformis)*
- ጫሪያ *(Pterocarpus lucens)*
- ሽመል *(Oxytenanthera abyssinica)*
- ዋልያ መቀር (*Boswellia papyrifera*)


የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አቅፎ የያዘ ሲሆን ይህን አካባቢ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደመቀነት ሆኖ በርሃማነት ወደ ሃገራችን እንዳይስፋፋ እየተከላከለ ያለውን አካባቢ ከማጠናከሩም በተጨማሪ የአየር ንብረት ሚዛን ለውጥ ለቋቋም የሚደረገውን ጥረት ከመደገፉም ባሻገር ሀገራችን ከካርቦን ንግድ ተጠቃሚ እንድትሆን ያስችላል። የታሳቢ

የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የአየር ንብረት ለወጥን (የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር) ለመከላከል የከባቢ አየርን ሙቀት በማመቅ ለውጥ የሚያመጣውን ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ በተክሎች አካል ውስጥ ሰብስቦ በማስቀረት ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ለአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክ በተወሰደው የጥናት (Vreugdenhil *et al*, 2012) ቀመር መሰረት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው 75.52 tCO_2e/ha በተክሎች አካል ውስጥ ሊቀር ይችላል፡፡ ስሌቱን መነሻ በማድረግ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ 1.44 $MtCO_2e$ አቅፎ ማስቀረት እንደሚቻል ተረጋግጧል፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ዓመታዊ የካርቦን ልቀት ጋር ሲነጻጸር 0.96 ፐርሰንት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ወደ ካርቦን ገበያ መግባት ቢችል ከ5.76 ሚሊዮን ዶላር ያላነሰ ገንዘብ ሊያስገኝ ይችላል፡፡ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው እንደ ጫብሊያ፣ ሲንሳና ኩድራ የመሳሰሉ ለምግብነት የሚየገለግሉ ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ በመሆኑ የገዳሙ ማህበረሰብ የምግብ ዋስትና እንዳይናጋ በተጠባባቂነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ውስጥ የሚገኙና በጥናት የተረጋገጡ የዕፅዋት ዝርያዎችን (ዕዝል አንድ) ላይ ተመልከቱ፡፡

አንድነት ገዳሙ አሁን ባለው የእጣን አመራረት በዓመት ከ500000/አምስት መቶ ሺህ/ ብር ያላነሰ ገንዘብ ከእጣን ምርት እያገኘ ቢሆንም የእጣን አመራረቱ ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑና ከአምራች ድርጅቶች የሚያገኙት ገቢ ዝቅተኛውን ፐርሰንት (ከ20% ያልበለጠ) በመሆኑ ገዳሙ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን የአመራረት ሂደቱ በገዳሙ ማህበረሰብ አባላት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ቢከናወን የገዳሙን ገቢ በሰፊው ሊደግፍ ከመቻሉም በላይ የተፈጥሮ ሃብቱን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዘላቂ ያደርገዋል፡፡

2.5 የውሃ ሀብት፡-

የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ የሰው ልጅ ለህልውናው የሚያፈልጉ የስነምህዳር ጥቅሞችና አገልግሎቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ ከእነዚህ የስነምህዳር አገልግሎቶች አንዱ በቂና ንጹህ ውሃ አመቱን በሙሉ ማግኘት ነው፡፡



ምስል 6. የስነምህዳር ጥቅሞች

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ጫና ውስጥ ቢሆንም እስካሁን የበረሰበትን ጫና በመቋቋም ተገቢውን የስነምህዳር አገልግሎት እያበረከተ የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ስፍራ ከስምንት በላይ የሚሆኑ ገባርና አብይ ወንዞች አመቱን በሙሉ ይፈሳሉ፡፡ እነዚህ ወንዞች ከመጠጥ አገልግሎት ባሻገር ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ የማልማት አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ወንዞች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራውና በዝቅተኛ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ተፋሰስ ለሚኖረው ማህበረሰብ የህልውና ዋስትና ሆነው ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥብቅ ስፍራ መጠበቅ በጥብቅ ስፍራው አካባቢ ላሉ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጀምሮ ከሀገር እስከሚወጡበት ያለውን ማህበረሰብ እያገለገሉ ሲሆን እነዚህ ወንዞች ከደረቁ በዚህ አካባቢ ለመኖር የማይታሰብ መሆኑን ጭምር ልንገነዘብ ይገባናል፡፡ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና አካባቢ የሚነሱ ወንዞች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የሚገኙ ወንዞች

የወንዙ ስም	የአዋሳኝ ቀበሌ ስም	የወንዙ መነሻ	የውሃው መድረሻ
ገንዳ ውሀ	አኩሻራ ቀበሌ		ዋና ወንዝ
ሸመል ውሀ	ሻሀርዳ ቀበሌ	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	የገንዳ ውሀ ገባር
ፈፋ ወንዝ	ቀበሌዎችን አያዋስንም	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	ገንዳ ውሀ ገባር
ሸንፋ ወንዝ	ኮዘራ ቀበሌ		ዋና ወንዝ
የሰይጣን ባህር	ሻሸጌ ቀበሌ	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	የማርያም ውሀ ገባር
ማርያም ውሀ	ሻሸጌ ቀበሌ	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	የሸንፋ ወንዝ ገባር
ሆደጥር	ሌንጫ ቀበሌ	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	የሸንፋ ወንዝ ገባር
ኩሻ ሸለቆ	ቀበሌዎችን አያዋስንም	ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው	የሸመል ውሀ ገባር

የማህበ ረስላሴ አንድነት ገዳም ቤተክርስቲያን በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ልዩ ቦታው መምህር አምባ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን በግዝት ክልሉ ውስጥ በተፈጥሮ የሚመነጭ ውሃ የለውም። በመሆኑም ከጥንት ጀምረው የገዳሙ አባቶች የዝናብ ውሃን በመገደብ ለተወሰነ ጊዜ ከተጠቀሙ በኋላ ከ4 ሰዓት በላይ በመንዝ ከወንዝ ውሃ በመቅዳት ሲጠቀሙ ቆይተዋል። ይህን ችግራቸውን በማየት በንግስት ዘውዲቱ መልካም ፈቃድ 1909 ዓ.ም የተሰራው የውሀ ማጠራቀሚያ ታንከርም በጣሊያን የአውሮፕላን ጥቃት እስከሚፈርስ ድረስ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። ይህ የውሀ ታንከር ከፈረሰበት ጊዜ ጀምሮ አዲሱ የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ እስከሚጠናቀቅ (1994 ዓም) ድረስ ከጉድጓድ ውሃና ከወንዝ ሲጠቀሙ ቆይተዋል። በክረምት ከዝናብ የሚያጠራቅሙትን የጉድጓድ ውሃ የአበው የውሃ (የአባቶች ውሃ) እያሉ የሚጠሩት ሲሆን ከዚህ ጉድጓድ ለሁለት ወራት ከተጠቀሙ በኋላ ሌሎችን ወራት በ10 በቅሎዎች ከሰይጣን ባህር እየቀዱ ሲጠቀሙ ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅት ገዳሙ አዲስ የውሀ ማጠራቀሚያ ገንዳ የገነባ ሲሆን ገንዳውም 6 ሜትር ጥልቀት፣12 ሜትር ርዝመትና 6 ሜትር ወርድ አለው፤ በመሆኑም 432 ሜትር ኩብ ውሀ የመያዝ አቅም ያለው ሲሆን አመቱን በሙሉ ከዚህ ጉድጓድ ይጠቀማሉ።



ምስል 7. በተለያዩ ዘመናት ያገለገሉና በማገልገል ላይ ያሉ የውሀ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች/Tankers/

2.6 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና አካባቢ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ሁኔታ

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ በሶስት ወረዳዎች (በመተማ፤በቋራና በጭልጋ) የሚዋሰንና እምቅ የብዝሀ ህይወት ሀብትባለቤት ሲሆን በውስጡም መነኮሳትንና የአካባቢውን ማህበረሰቦች አቅፎ ይገኛል፡፡ አካባቢው በብዝሀ ህይወት ሀብቱ የተሻለ በመሆኑ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ፤በጥብቅ ስፍራውና አዋሳኝ ቀበሌዎች ድንበር አመቱን በሙሉ የሚፈሱ ወንዞች በመኖራቸው እንስሳትና የአካባቢው ነዋሪዎች የጎላ የውሀ ችግር የለባቸውም፡፡

2.6.1 የገዳሙ የገቢ ምንጮች

ገዳሙ የሚተዳደረው በእርሻ፤ በቀንድ ከብት እርባታ፤በእጣን ምርት፤ በማር ምርት፤ በፍራፍሬ ምርትና በቤት ኪራይ ሲሆን የገዳሙ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ሰብል ነው፡፡

1. **ሰብል ልማት፡-** በገዳሙ ውስጥ ለአመታዊ ፍጆታ የሚመረቱት የሰብል አይነቶች ማሽላና ሰሊጥ ሲሆኑ እነዚህ ሰብሎች የሚመረቱት አመታዊ ፍጆታን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከ200-300 ሄክታር የሚገመት መሬት በእያመቱ በሰብል ይሸፈናል፡፡ የሰብል ማምረት ስራ የሚከናወነው መስራት በሚችሉ የገዳሙ አባቶችና ከገዳሙ አካባቢ በሚኖሩ መሬት የሌላቸው አ/አደሮች ሲሆን ከ 22-28 የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ከውጭ በእርሻ ስራው ላይ ይሳተፋሉ፡፡ በመሆኑም ገዳሙ ከላይ ቁጥራቸው ለተገለጸው የአካባቢው ነዋሪዎች የስራ እድል የፈጠረ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡ በእርሻ እንቅስቃሴው ላይ ወደፊት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ የአካባቢው ነዋሪ የመሬት ፍላጎትና ገዳሙ ውሥጥ ገብቶ የማረስ አዝማሚያ ከፍተኛ ስለሆነ ከብዝሀ ህይወት ጥበቃው ጋር የተጣጣመና ዘላቂ ጥቅም እንዲያስገኝ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአጠቃቀም ቀጠና /utilization zone/ ተለይቶ ማኔጅመንት ፕላን ሊዘጋጂለት ይገባል፡፡

2. **እንስሳት እርባታ፡-** ገዳሙ በ2ኛ ደረጃ የመተዳደሪያ ገቢ የሚያገኘው ከእንስሳት እርባታ እንደሆነ የገዳሙ አባቶች ያስረዳሉ፡፡ የገዳሙ የከብቶች ቁጥር የጠራ መረጃ ባይኖርም ቁጥሩ ከ3000 በላይ የሚሆን የቀንድ ከብቶች እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ በገዳሙ ውስጥ እየረቡ ያሉት የአካባቢ የቀንድ ከብት ዝርያዎች የተሻለ ተክለ ቁመና ያለቸውና ምርታማም እንደሆኑ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ፡፡ እነዚህን ከብቶች በበላይነት የሚንከባከብ እንደ ከብቶቹ እድሜና ጾታ የማዕረግ ስም ይሰጠዋል፡፡ የበሬና የላም የበላይ ኃላፊዎች በሬ እራስና ላም እራስ ይባላሉ፡፡ በገዳሙ ውስጥ 40 የሚሆኑ የቀንድ ከብት የጥበቃ ሰራተኞች (እረኞች) ያሉ ሲሆን እነሱም

የገዳሙን ከብቶች ከቦታ ቦታ ይዘው በመንቀሳቀስ ይመግባሉ፡፡ የከብቶች አመጋገብ በልቅ ግጦሽ ከቦታ ወደ ቦታ በማንቀሳቀስ ብቻ የተወሰነ ስለሆነ አመቱን በሙሉ እንስሳት በደኑ ውስጥ የሚበቅለውን ሳር ይጠቀማሉ፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የጫካ ማር ለመቁረጥ፣ ምንጥር ለማቃጠልና አዲስ ሳር እንዲበቅል በማለት ሆን ተብሎ የሚለኮስ ሰደድ እሳት የእንስሳትን የመኖ አቅርቦት እየተፈታተነው ይገኛል፡፡ ገዳሙ ወንድ ከብቶችን ለእርሻ አገልግሎት ይጠቀምባቸዋል፡፡ ላሞች የተሻለ ወተት እንዳላቸው ቢገለጽም የሚታለቡት ከሐምሌ እስከ ጥቅምት ወር ሲሆን የሚጠራቀመው ቅቤም ለውስጥ ፍጆታ ብቻ የሚውል ነው፡፡

ሌለው ጉዳይ ገዳሙ ለእርሻ የደረሱ ወይፈኖችን በመለየት አቅንተው እንዲያርሱ ለገዳሙ አካባቢ ነዋሪዎች በነጻ ለአንድ ክረምት ይሰጣል፡፡ ከሰብል ምርት በተጨማሪ ገዳሙ የቀንድ ከብቶችን በመሸጥ ይጠቀማል፡፡ ሌላው ገዳሙ ለውሃ መቅጃ፣ ለእህል መጫኛና አሁን እየተገነባ ላለው የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የግንባታ ቁሳቁስ መጫኛ የሚጠቀምባቸው 30 የሚሆኑ አህዮች አሉት፡፡ እነዚህን የሚጠብቁ 2 እረኞች ያሉ ሲሆን በበላይነት የሚያስተዳድር ሰው አህያ ራስ ተብሎ ይጠራል፡፡

3. የእጣን ምርት፡- ገዳሙ በ3ኛ ደረጃ በገቢ ምንጭነት የሚጠቀመው በገዳሙ የደን ክልል ውስጥ ያለውን የእጣን ዛፍ ለእጣን አምራች ድርጅቶች ኮንትራት በመስጠት ሲሆን ከዚህ ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት የሚቻል ቢሆንም የሚፈለገውን ያክል ጥቅም እየገኙ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ያለው የአመራረት ሥልት ሳይንሳዊ ያልሆነና ዘላቂነት የሌለው በመሆኑ የእጣን ዛፎች እየደረቁ ስለሆነ ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ ዘላቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ከእጣን ምርት የሚገኘው ገቢ የአመታዊ የሰብል ምረት ፍጆታ ክፍተታቸውን ለመሙላትና ሌሎች ለገዳሙ የሚያስፈልጉ ግብአቶችም ለመግዛት ይጠቀሙበታል፡፡

4. ንብ እርባታ፡- ከእጣን ምርት በተጨማሪ ገዳሙ ከሚያካሄደው የባህላዊ ንብ እርባታ ስራ የገዳሙን ማህበረሰብ ፍጆታ ይሸፍናል፡፡ ገዳሙ ከ1995/6 ዓም ጀምሮ በባህላዊ መንገድ የንብ እርባታ ስራ የጀመረ ሲሆን በዚህ ዘርፍ የተጀመረው ስራ በስፋት ከተሰራበት ከፍተኛ ውጤት የሚገኝበት እንደሆነ በመስክ ምልከታችን ማረጋገጥ ችለናል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ለገዳሙ የሚያስፈልገውን በቂ ሰም በራሳቸው የንብ እርባታ ስራ ከሚያገኙት የንብ ውጤት በማምረት እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ ገዳሙ ለንብ እርባታ ስራ በከፍተኛ ደረጃ ተስማሚ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከአንድ ባህላዊ ቀፎ እስከ 25 ኪግ እንደሚመረት በስራው የተሰማሩ አባቶች ይናገራሉ፡፡

አሁን ያሉት ከ70 በላይ የሚሆኑ ባህላዊ ቀፎዎች የንብ መንጋ አያያዝም ከዘርፉ ወደፊት ከፍተኛ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል የሚያመላክት ነው።



ምስል 8. የማነበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የንብ እርባታ

ከላይ ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች በተጨማሪ በ1989 ዓም በእርዳታ ከተገኘች አንድ የእህል ወፍጮና ማህበሩ ከተከለው ሌላ አንድ የእህል ወፍጮ በሚያገኘው ገቢ ያለበትን የአመታዊ የምግብ ፍጆታ ክፍተት ይሸፍናል።

5. የመስኖ ልማት፡- ገዳሙ ገርድም ከሚባለው ሞፈር ቤት ከጀመረው የቋሚ አትክልት ልማት የተወሰነ ገቢ እያገኘ ቢሆንም ገዳሙ ካለው የውሃ ሃብትና ምቹ የልማት ቦታ ጋር ሲነጻጸር በጣም ሰፊ ስራ ይጠይቃል። የቋሚ አትክልት ልማቱ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን የደን ልማት የሚያግዝ ከመሆኑም ባሻገር ለገዳሙ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የመሆን አቅም አለው። ለዚህ ልማት አዋሳኝ ወረዳዎች (ቀበሌዎች) በቋሚ አትክልት ልማቱ ላይ ምንም አይነት ድጋፍ እያደረጉላቸው አይደለም። በመሆኑም ወደፊት ከወረዳና ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤቶች ከፍተኛ የግብዓትና የሙያ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ገዳሙ በአጠቃላይ ከ40 በላይ ለሚሆኑ የጉልበት ሰራተኞች ያሉት ሲሆን አንድ የጉልበት ሰራተኛ ዘጠኝ ወር ሲያገለግል አንድ የአመት ወይፈን ይሰጠዋል።

2.6.2 የመናኝ አባቶች የስራ ክፍፍልና የስራ ባህል

በአሁኑ ሰዓት በዚህ ገዳም ውስጥ ከ250 በላይ የሚሆኑ አባቶች የሚኖሩ ሲሆን እነዚህ አባቶች የገዳሙን ስርዓት ጠብቀው ይኖራሉ። በገዳሙ ውስጥ ያሉት አባቶች ቀኑን ሙሉ በስራ

የተጠመዱና የተሰጣቸውንም ስራ በከፍተኛ ተነሳሽነት የሚፈጽሙ ናቸው። በገዳሙ ውሥጥ መነኮሳት ዘወትር ከሚያከናውኑት የሀይማኖት ግዴታ በተጨማሪ መጋቢ የሚሰጣቸውን የልማት ስራ ማለትም የደን ልማትና ጥበቃ ስራ፣ የእንስሳት እርባታ ስራ፣ የሰብል ልማት ስራ፣ የመስኖ ልማት ስራ፣ የንብ ማነብ ስራ፣ የምግብ እህሎችን የማጓጓዝ፣ የመፍጨትና የማብሰል ስራ፣ ውሀ የመቅዳት ስራ በተነሳሽነትና ከልብ በመነጨ ፍቅር ይሰሩታል። በገዳሙ ውሥጥ ያሉት አባቶች የሚሰጣቸውን ስራ እኔ ልስራው እኔ ልስራው በማለት ይሽቀዳደማሉ።

1. **የገዳሙና የአካባቢው ነዋሪ ግንኙነት፡-**

ገዳሙ ከተወሰኑ አጥፊ ግለሰቦች ውጭ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት አለው። የአካባቢው ማህበረሰብ ለገደሙ የተለያዩ የጉልደበት ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል። በአመት ሁለት ጊዜ ከ80-90 የሚሆን የአካባቢው ነዋሪ በመስከረም ወር ካንቻ በመምታትና በታህሳስ ወር ሰብል በመሰብሰብ ለገዳሙ የጉልበት ድጋፍ ያደርጋሉ። በእነዚህ ሁለት ጊዜያት ለሚያደርጉት ድጋፍ የላብ ማድረቂያ ከገዳሙ በሬዎች መርጠው አንድ አንድ በሬ እንዲያርዱና እንዲመገቡ ይሰጣቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ አሁን ለሚሰራው ህንጻ ቤተክርስቲያን የግንባታ ቁሳቁስ በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። የገዳሙ አባቶችም የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተማርና የተጣላ በማስታረቅ በአካባቢው ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር የሚያደርጉት አስተቃጽኦ ከፍተኛ ነው። በእያመቱ የካቲት 27 ቀን ስለታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ሀይማኖታዊ፤ ስነምህዳራዊና ማህበራዊ ጥቀሞች ከማህበረሰቡ ጋር የሚካሄደው የትምህርትና ቅስቀሳ ውይይት የማስበረሰቡን ግንዛቤ እያሳደገው እንደሆነ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ። የአካባቢው ማህበረሰብም ለገዳሙ አባቶች ከፍተኛ አክብሮት አለው።

2. **በገዳሙ ዉስጥ የሚታዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፡-**

በገዳሙ ውስጥ በዳሰሳ ጥናቱ ወቀት የታዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች

1. ግዝት ክልሉ ውስጥ ያሉ መናንያን አመቱን በሙሉ የሚጠቀሙበት የመጠጥ ውሀ በክረምት ወቅት ያጠራቀሙትን ዝናብ ውሀ ነው። ሆኖም ግን አካባቢው ሞቃት ስለሆነ መናንያንን ለተለያዩ የውሀ ወለድ በሽታዎች ሊዳርጋቸው ይችላል።
2. ገዳሙ በ2ኛ ደረጃ ገቢ የሚያገኘው ከእንስሳት እርባታ መሆኑን ከላይ መግለጻችን ይታወቃል። ሆኖም ግን እንስሳት ተገቢውን ውጤት እንዳይሰጡ ማነቆዎች አሉባቸው። በገዳሙ ውስጥና አካባቢ የቀንድ ከብቶችን አካል የማቁሰልና ለሞት የሚዳርግ የቀንድ ከብት በሽታ በስፋት ስላለ በገዳሙ የቀንድ ከብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ

ይገኛል። ሆኖም ግን እስካሁን ድረስ ዘመናዊ ህክምና እያገኙ አይደለም። በመሆኑም እስካሁን ባለው ሁኔታ በበሽታው የሚያዙ እንስሳት በአብዛኛው እየሞቱ እንደሆነ በዚህ ዘርፍ ከተሰማሩ የገዳሙ አባቶችና የማህበረሰብ ክፍሎች ለማረጋገጥ ችለናል።

3. ሌላው እነዚህ የቀንድ ከብቶች አመቱን በሙሉ የሚመገቡት በልቅ ግጦሽ ብቻ እንጅ በተበይነት ደረጃ የተሰበሰበ ድርቆሽና ተረፈ ምርት አያገኙም። በመሆኑም አሁን ካለው የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ነዋሪዎች የልቅ ግጦሽ ጫና ጋር ተያይዞ በሚዚያና በግንቦት ወር የመኖ ክፍተት መኖሩን ለመረዳት ችለናል። በመሆኑም የድርቆሽ ሳር በተገቢው ሰዓት ሊሰበሰብላቸው ይገባል፤ ከውጭ ያለው ከፍተኛ የልቅ ግጦሽ እንቅስቃሴም መፍትሄ ሊያገኝ ይገባዋል።
4. ሌላው ጉዳይ ገዳሙ በርካታ የወተት ላሞች እያረባ ሲሆን እነዚህ ላሞች ከአካባቢው ዝርያ የተለዩና የተሻለ ምርት እንደሚሰጡ አባቶች ይናገራሉ። ሆኖም ግን ከእነዚህ ላሞች የሚገኘው ወተትና የወተት ውጤት አጥጋቢ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ችለናል። የከብቱ ቁጥር በውል ባይታወቅም ከ3000 በላይ የቀንድ ከብት ባለበትና ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር ላሞች በያዙበት ቦታ እስካሁን የሚገኘው ወተትና የወተት ውጤት ከገዳሙ ፍጆታ ያለፈ አይደለም። ለዚህ ውጤት መቀነስ ምክንያቱ ከመኖ እጥረት የተነሳ ላሞችን አመቱን በሙሉ ማለብ አለመቻሉ አንዱ ሲሆን በቂ መኖ ባለበትና በሚታለብበትም ወቅት የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ ማሽን ባለመኖሩ የተነሳ የሚፈለገውን ውጤት ማግኘት አልተቻለም።
5. ሌላኛው ችግር በገዳሙ ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው እንቡልቡል ከሚባለው አካባቢ በህገወጥ መንገድ ሰፍረው የነበሩና ትክ መሬት ተሰጥቷቸው እንዲወጡ የተደረጉ 70 አ/አደሮች ጉዳይ ነው። እነዚህ አ/አደሮች ወደ ገዳሙ ሲገቡ ቁጥራቸው 8 እንደነበሩና ሌሎች ህገወጥ ሰፋሪዎችን በተለያየ የዝምደና ትስስር ወደ ቦታው በመሳብ አሁን ቁጥራቸው ከላይ ወደ ተጠቀሰው ቁጥር ሊያሻቅብ እንደቻለ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ። ከእነዚህ አ/አደሮች ከፊሎች ትክ መሬት የተሰጣቸው ሲሆን ሌሎች የተወሰኑ አ/አደሮች እስካሁን ትክ መሬት ያልተሰጣቸው እንዳሉ ከቀበሌው አመራሮች ለማረጋገጥ ችለናል። አ/አደሮች በገዳሙ ውስጥ የሚያካሄዱትን የሰብል ምርት ስራ ያቋረጡ ቢሆንም ከብቶቻቸውን ሲያሰማሩ እንደቆዩና ወደፊትም በዚሁ ሁኔታ እንቀጥላለን የሚል አመለካከት እንዳላቸው በጥናቱ ወቅት አረጋግጠናል። አንዳንዶች እንዲያውም ወደ ገዳሙ (አንቡልቡል) እንመለሳለን የሚል ዝንባሌ እያሳዩ እንደሆነ ትክ መሬትም ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ለመረዳት ችለናል። ውጭ የሚሰጣቸው ትክ መሬት

ትኩረት ተሰጥቶት በአጭር ጊዜ ውስጥ ካልተፈታ ውሎ ሲያድር የመራት እጥረት ስለሚፈጠር ሌላ የመልካም አስተዳደር ችግር ማምጣቱ አይቀርም::

6. ሌላው ችግር የዱር እንስሳት አደንና ሰደድ እሳት ሲሆኑ የጥብቅ ስፍራውን ህልውና እየተፈታተኑት ይገኛሉ፡፡ በጥናቱ ወቅት በመስክ በምንቀሳቀስበት ጊዜ ከፍተኛ የሰደድ እሳት ቃጠሎ የታየ ሲሆን የዱር እንስሳትንም ለማደን ተደጋጋሚ የመሳሪያ ፍንዳታ ይሰማ ነበር፡፡
7. ቦታው ሞቃት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከበጋ ወቅት ይልቅ በመክረምት (በዝናብ) ወቅት የገዳሙ ብዝሀህይወት ሀብትና መልከዓ-ምድራዊ ገጽታ የበለጠ ቀልብን የሚማርክና በበርካታ ሰዎች ሊጎበኝ የሚችል ቢሆንም ከደረቅ አባይ እስከገዳሙ ያለው የጠጠር መንገድ በአግባቡ ስላልተሰራና ወደ ገዳሙ ክልል ለመሻገር በገንዳ ውሃ ወንዝ ላይ ድልድይ ስላልተሰራለት በክረምት ወቅት ገዳሙን ለመጎብኘት የሚፈልጉ ጎብኝዎች መጎብኘት አለመቻላቸው ሌላው ችግር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመንገዱ አለመሰራት በጥብቅ ስፍራው ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለምሳሌ የእሳት ቃጠሎን ቶሎ ደርሶ መፍትሔ ለመስጠትም እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

8. ከሌሎች አጎራባች ወረዳዎቸችና ቀበሌዎች የሚመጡ ዘላኖችን ለመከላከልና ልቅ ግጦሽን ለመቀነስ እየተደረገ ያለው ጥረት አጥጋቢ ባለመሆኑ ከጭልጋ፣ከአለፋ፣ ከጣቁሳ፣ከቋራና ከመተማ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ወደ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ልቅ ግጦሽ በማሰማራት ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆናቸው፡፡ገዳሙ ከሚያረባቸው እንስሳት በተጨማሪ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚኖሩ አ/አደሮችና አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ቁጥር ያለው የቀንድ ከብትና ፍየል ወደ ገዳሙ ስለሚያሰማሩበት የእንስሳቱ ቁጥር ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የመሸከም አቅም በላይ ሆኗል፡፡ ሌላው በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚኖሩት አ/አደሮች የሰፈሩበት አካባቢ ሲጎዳ፣ ለእንስሳታቸውና ለኑሮ አልመቻቸው ሲል ድንበሩን ተከትለው በመንቀሳቀስ ከፍተኛ ጥፋት እያደረሱ ይገኛሉ፡፡

2.6.3 የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች ሶሽዮ ኢኮኖሚ

የማህበረ ስላሴን አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ከአምስት ቀበሌዎች ጋር ይዋሰናል፡፡ እነሱም ሻሸጌ፣ አኩሻራና ሌንጫ ከመተማ ወራዳ፣ ኮዘራ ከቋራ ወረዳና ሻሃርዳ ከጭልጋ ወረዳ በኩል ያዋስኑታል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ አሰፋፈር የተበተነ ሲሆን የሳርና

የቆርቆሮ ቤቶችን ለመኖሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ የአዋሳኝ ቀበሌዎች ሶሽዮ ኢኮኖሚ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

1. የአዋሳኝ ቀበሌዎች የህዝብ ብዛት፡- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ቀበሌዎች ያለውን የህዝብ ቁጥር ለመተንተን አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም በህጋዊና በህገወጥ ሰፈራ ምክንያት በየጊዜው ቁጥሩ ስለሚጨምር ነው፡፡ በ2001ዓም በተካሄደው የህዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት የመተማ ወረዳ የህዝብ ቁጥር በ994 ዓም ከነበረው ከመቶ እጥፍ በላይ የጨመረ ሲሆን የቋራ ወረዳ ደግሞ ከ164 እጥፍ በላይ ጨምሯል፡፡ አሁንም ቢሆን የአዋሳኝ ወረዳዎች የህዝብ ቁጥር ከሌሎች አካባቢዎች የህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ እንደሆነ ቢገለጽም በእነዚህ ስፍራዎች በከፍተኛ ፍጥነት የህዝቡ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ በዝምድና፣ በጋብቻ፣ በአበልጅና በተለያዩ ትስስሮች ከሌሎች አካባቢዎች ሰዎች እየመጡ ስለሚሰፍሩ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡ ከአዋሳኝ ቀበሌዎች ወረዳ ገ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት ባገኘነው መረጃ መሰረት የ2006ዓም የአምስቱ ቀበሌዎች የህዝብ ብዛት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ የማህበረሰላሴ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ ቀበሌዎች የህዝብ ብዛት

ተ.ቁ	የቀመሌው ስም	የህዝብ ብዛት		
		ወንድ	ሴት	ድምር
1	ሻሸጌ	2984	2513	5497
2	ሌንጫ	1679	1242	2921
3	አኩሻራ	2114	1886	4000
4	ሸሃርዳ	1861	1744	3605
5	ከዘራ	1808	1594	3402
	ድምር	8638	7385	19425

በአዋሳኝ ከበሌዎች ከሚኖረው ማህበረሰብ ውስጥ 62% የሚሆነው ወንድ ሲሆን አብዛኛው የዚህ የማህበረሰብ ክፍል የአካባቢውን ደን በመጨፍጨፍ በእርሻ ስራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡

2. የአዋሳኝ ቀበሌዎች የገቢ አማራጮች፡- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ከሰብል ልማት፣ ከእንስሳት እርባታ፣ ከንግድ፣ ከማር ምርት፣ ከደን ውጤቶች

ሽያጭ፣ ከፍራፍሬና ከቀን ስራ ገቢ እንደሚያገኙ ይናገራሉ፡፡ በእነዚህ ቀበሌዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች በዋናነት የሚተዳደሩት በሰብል ልማትና በእንስሳት እርባታ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ሰብል ልማት፤- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ሰብል በገቢ ምንጭነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ሰብል የሚመረተውም ለቤት ፍጆታና ለገበያ እንደሆነ በጥናቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የእርሻ ስራ ለመስራት በአካባቢው አልፎ አልፎ ከሚከሰተው የዝናብ እጥረት ውጭ የመሬት እጥረት እንደሌለ በመስክ ምልከታችን ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ከሚመረቱ ሰብሎች መካከል ማሽላ፣ጥጥ፣ ሰሊጥ፣ ዳጉሳ፣ ጤፍ፣ ለውዝና ቦለቄ ዋና ዋና ናቸው፡፡ ጤፍ በአብዛኛው ለፍጆታ የሚመረት ሰብል ሲሆን ሰሊጥ፣ ጥጥ፣ ቦለቄና ለውዝ ለገበያ የሚመረቱ ሰብሎች ናቸው፡፡ ማሽላ ደግሞ ለፍጆታና ለገበያ ይመረታል፡፡

በማህበረሰላሴ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚመረቱ ዋናዋና የሰብል አይነቶችና አገልግሎታቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ.3፡ በማኅበረሰላሴ ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራና አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚመረቱ ዋናዋና የሰብል አይነቶችና አገልግሎታቸው

ተቁ	የሰብል አይነት	ምርታማነት በኩ/ል	የአካባቢ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ	አገልግሎት
1	ማሽላ	10-26	480.00	ለፍጂታና ለሽያጭ
2	ጥጥ	8-30	1480.00	ለሽያጭ
3	ሰሊጥ	2-5	3700.00	ለሽያጭ
4	ዳጉሳ	8-12	600.00	ለፍጆታ
5	ጤፍ	7-12	1200.00	ለፍጆታ
6	ቦለቄ	12-30		ለሽያጭ
7	ለውዝ	20-25	2200.00	ለሽያጭ
8	በቆሎ	28	380.00	ለፍጂታና ለሽያጭ
	በርበሬ	26	1800.00	ለፍጂታና ለሽያጭ

እንስሳት እርባታ፡- እንስሳት በተለይም የቀንድ ከብቶችና ፍየሎች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ በስፋት ይረባሉ፡፡ አካባቢውም ለእነዚህ እንስሳት እርባታ በጣም ተስማሚ ነው፡፡ እነዚህ

እንስሳት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጡ የአካባቢው ህብረተሰብ የገቢ ምንጮች ናቸው። በመሆኑም በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ የሚኖሩ አ/አደሮች ከእነዚህ እንስሳት ጋር ያላቸው ትስስር ከፍተኛ ሲሆን ለእነዚህ እንስሳት ግጦሽ የሚሆን መሬትም በአሁኑ ወቅት በእነዚሁ አካባቢዎች ይገኛል። ሆኖም ግን ይህ የግጦሽ መሬት በህገወጥ ሰፋሪዎችና በአካባቢው ነዋሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት እየተመነጠረ ወደ እርሻ መሬትነት እየተቀየረ ይገኛል። ለዚህ ችግር መከሰት መንስኤው በእነዚህ አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚኖሩ የአ/አደሮች የመሬት ይዞታ በአግባቡ አለመለየቱ ነው። ስለዚህ በዚህ አካባቢ ጉልበት ያለው አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ እየመነጠረ ማረስ ይችላል። በመሆኑም ህገወጥ እርሻው በዚሁ ሁኔታ ከቀጠለ የእንስሳት የግጦሽ መሬት በሙሉ ወደ እርሻ መሬት ሊለወጥ ይችላል። በህገወጥ አራሾች የግጦሽ መሬቶች ወደ እረሻ መሬት መቀየራቸው የመኖ እጥረት እንዲኖር በማድረግ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ የሚኖሩ አ/አደሮች እንስሳትን ወደ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው እንዲያሰማሩ ያደርጋል። ከሰብል ተረፈ ምርት ውጭ የድርቆሽ ሳር በተበይነት ደረጃው የአካባቢው አ/አደር ለእንስሳት መኖነት ማሰባሰብ የተለመደ አይደለም። በመሆኑም የእንስሳት እርባታ ሙሉ በሙሉ በልቅ ግጦሽ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም ከበጋዎቹ ወራት መጨረሻ ላይ የሚፈጠረውን የመኖ እጥረት ለመቅረፍ የዛፍ ቅርንጫፎችን እየቆረጡ ይመግባሉ። ይህን ችግር ለመቅረፍ አ/አደሮች በአካባቢው ያለውን የመኖ ሳር በወቅቱ እንዲያሰባስቡ ማስቻል ተገቢ ነው።

በእንስሳት እርባታ ዘርፍ ላይ ካለው የመኖ እጥረት በተጨማሪ የእንስሳት በሽታ ከዘርፉ የሚገኘውን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳው ይገኛል። በአካባቢው በስፋት የሚከሰቱ የእንስሳት ጤና ችግሮች በአርሶ አደሮች አገላለጽ ገንዲ፣ ምታት፣ ገጭታ፣ወተቴና አፈማያዝ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ህክምና ከሚያገኙት የማያገኙት ይበልጣሉ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት እንስሳት በተጨማሪ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ዶሮ በከፍተኛ ደረጃ የሚረባ ሲሆን በገቢ ምንጭነቱ ቀላል የማይባል ድርሻ አለው። በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ለየት ያሉ መቀትን የሚቋቋሙ የዶሮ ዝርያዎች በስፋት ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ምንጫቸው ከየትና እንደት ለማዳ እንደሆኑ የጠራ መረጃ በጥናት ወቅት ባይገኝም በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ቀበሌዎች የሚገኙ አ/አደሮች ከሚያረቧቸው ጅግራዎች ከፍተኛ ቁጥር ያለው እንቁላል እንደሚያገኙና የእንቁላሉም ዋጋ ከዶሮ እንቁላል ዋጋ እጥፍ እንደሆነ ይናገራሉ።

የማር ምርት፡- ሌላው የገቢ ምንጭ ማር ሲሆን አካባቢው የተሻለ የደን ሽፋን ያለው በመሆኑና አመቱን በሙሉ አበባ የሚገኝበት አካባቢ በመሆኑ ለንብ እርባታ ስራ ምቹ ነው፡፡ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ቀበሌዎች ከ3600 በላይ ንብ መንጋዎች ያሉ ሲሆን በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ የሚረቡ ናቸው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች አንዱ የገቢ ምንጭ ማር ቢሆንም ከአለው እምቅ አቅም አንጻርና ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ጋር ካለው ተስማሚነት አኳያ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ የሚባል ስለሆነ በዚህ ዘርፍ ላይ ወደፊት በስፋት ሊሰራበት ይገባል፡፡

ሠንጠረዥ.4፡ የማህበረሰላሴ ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ ቀበሌዎች የቤት እንስሳት ቁጥር

ተቁ	የእንስሳት አይነት	አዋሳኝ ቀበሌዎች					
		ሻሸጌ	ሌንጫ	አኩሻራ	ሸሃርዳ	ኮዘራ	ጠቅላላ ድምር
1	የቀ/ከብት	23215	25470	14727	10309	6935	80656
2	ፍየል	5175	7735	5882	3755	4280	26827
3	በግ	3850	5215	4906	309	480	14760
4	አህያ	905	570	478	605	175	2733
5	በቅሎ	7	0	7	17	0	31
6	ግመል	3	0	0		14	17
7	ደሮ	6970	19515	4044		9248	39777
8	ዘ/ቀፎ	3	9	35			47
9	ባ/ቀፎ	1800		895	639	260	3594

የደን ውጤቶች፡- በዚህ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከደን ውጤቶች ማለትም ከእጣን ምርትና ክሰል በማክሰል ተጨማሪ ገቢ እንደሚያገኙ ከአካባቢው ሰዎችና በጥናቱ ወቅት ከመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ እነዚህ የደን ውጤቶች አብዛኛውን ጊዜ በህገውጥ መንገድ የሚመረቱ በመሆናቸው በደን ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም እያደረገ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ አካባቢዎች የሚመረተው የክሰል ምርት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ የወረዳ ከተሞችና ወደ መሀል አገር የሚጫን ሲሆን የመኪና መንገዶችን ተከትሎ ከፍተኛ የክሰል ምርት ለገበያ እንደሚቀርብ በመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ የአዋሳኝ ቀበሌዎች የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ያለው የህዝብ ቁጥር በህገወጥ ሰፈራና

ባለው ከፍተኛ የመዋለድ መጠን የተነሳ በተፈጥሮ ሀብቱ ላይ ከፍተኛ ጥፋት እያደረሰበት ይገኛል። በእነዚህ ቀበሌዎች ያለው የመሬት ይዞታ በአግባቡ ተቆጥሮ የተመዘገበ ባለመሆኑ ጉልበት ያለው የቻለውን ያክል የተፈጥሮ ደኑን መንጥሮ ወደ እርሻ መሬት መለውጥ ይችላል።

በበታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝ ቀበሌዎች ከፍተኛ የሆነ የእጣን ዛፍ ሀብት ያለበት ቢሆንም የእርሻ መሬት ለማግኘት ሲባል በሚደረግ የደን ጭፍጨፋና ተገቢ ባልሆነ የእጣን ዛፍ ማድማት ምክንያት በከፍተኛ ፍጥነት ከአካባቢው ዝርያው እየጠፋ ይገኛል። በተመሳሳይ ሰው የሚመገባቸው የዱር እንስሳት በሙሉ ከአካባቢው በአደን ምክንያት እየጠፉ ይገኛሉ። በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ያለው ከፍተኛ የደን ጭፍጨፋ፣ የዱር እንስሳት አደን፣ ህገወጥ እርሻ፣ የክሰል ምርት የብዝሀ ህይወት ሀብቱ (የዱር እንስሳትና እጽዋት) በእልቂት አደጋ ውስጥ እንዲገኙ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ የቆላ አጋዘንን ብንመለከት ከአዋሳኝ ቀበሌዎች የጠፋ ሲሆን በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ልዩ ቦታው ግዝት ክልል በተባለው አካባቢ ብቻ የሚኖሩ ሲሆን በዚህ አካባቢ የሚኖሩትም ቁጥራቸው ከአስር አይበልጡም።

እያንዳንዳቸው ብቸኛ ዝርያዎች ሌሎች ብቸኛ ዝርያዎች እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ብቸኛ ዝርያዎች ሲጠፉ ሌሎች ከእነዚህ ብቸኛ ዝርያዎች ጋር ትስስር ያላቸው ዝርያዎች ይጠፋሉ። ይህ አይነቱ የብዝሀ ህይወት መጥፋት የብዝሀ ህይወት የጥፋት ሰንሰለት ተብሎ ይጠራል። ለዚህም ማረጋገጫ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ ያሉት የብዝሀ ህይወት ሀብቶቻችን በመሚጠጣቸው ከአካባቢያቸው ተነስተው በእነዚህ አካባቢዎች እንዲሰፍሩ ተደርገዋል። አሁንም ቢሆን በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ አካባቢ ያሉ ህይወታዊ ሀብቶች ዘላቂነት በሌለው አጠቃቀም የተነሳ በጥፋት አደጋ ውስጥ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከሰደድ እሳትና ከጭፍጨፋ የተረፉ በርካታ የተፈጥሮ ደኖች ያሉ ቢሆንም በአካባቢው ያለው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም በህግና በስርዓት የማይመራ ከሆነ ነገ ተነገ ወዲያ ከዚህ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ወስዳችሁ አስፍሩን የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው። በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ደኖች የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታትና በአካባቢው ያለውን የስነ-ምህዳር ሚዛን በመጠበቅ ሰውና ሌሎች እንስሳት በአካባቢው እንዲኖሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። ደኖች ለአካባቢ ሙቀት መጨመር ዋና ምክንያት የሆነውን የካርበን ልቀት በመቀነስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ገቢዎች በተጨማሪ በቁም ከብት ንግድና በቅባት እህሎች ንግድ ገቢያቸውን እንደሚደጉሙ ይናገራሉ።

3. በአዋሳኝ ቀበሌዎች ያሉ ዋና ዋና ችግሮች፡- በጥናቱ ወቅት በአዋሳኝ ቀበሌዎች በምንቀሳቀስበት ጊዜ ያየናቸው ዋናዋና ችግሮች

- ከዚህ በፊት ያሉ ጥናቶች ከፍተኛ የደን ሀብት እንዳሉ ቢገልጹም በሰደድ እሳትና በምንጣሮ የተነሳ ከፍተኛ የደን ሀብት እየጠፋ ሲሆን ይህን ድርጊት ለማስቆም የሚመለከታቸው የቀበሌና የወረዳ መ/ቤቶች ትኩረት አደርገው እየሰሩ አይደለም፡፡ አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ ዛፍ የሚቆርጥበት ምሳርና የሚያድንበት መሳሪያ ሳይዝ ወደ ጫካ አይገባም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልቅ ግጦሽና የዱር እንስሳት አደን እንዲሁ የብዝሀ ሕይወት ሀብቱን እየተፈታተኑት ይገኛሉ፡፡
- የአካባቢው የመሬት ይዞታ በአግባቡ ያልተቆጠረ በመሆኑና የመንግስት /የወል/ ይዞታዎችን የሚከታተል አካል ባለመኖሩ የተነሳ ከማንኛውም አካባቢ የመጣ ግለሰብ በእነዚህ የወል መሬቶች ላይ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት አቅሙ እስከፈቀደ በመጨፍጨፍ ወደ እርሻ እየቀየራቸው ይገኛል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው አ/አደር ከ10 ሄክታር ሊኖረው እንደሚችል ከሻሸጌ ቀበሌ አመራሮች ለመረጋገጥ ችለናል፡፡ አንዳንድ አካባቢዎችና ቀበሌዎች ላይ ደግሞ በመሬት ሻሚያ ከፍተኛ የሆነ የእጣን ዛፍ ደን እየተጨፈጨፈ ይገኛል፡፡ በሻሸጌ ቀበሌና በአለፋ ወረዳ ድንበር ያለውን የእጣን ዛፍ ደን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡
- ሙያዊ ባልሆነ የእጣን ምርት አመራረት የተነሳ በአዋሳኝ ቀበሌዎች ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእጣን ዛፍ እየደረቀ ይገኛል፡፡ አንድ የእጣን ዛፍ 28 ቦታ ላይ መድማቱን በመስክ ምልከታችን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ በአብዛኛው የእጣን ዛፍ ከስር ተተኪ ችግኝ የሌለው በመሆኑ ሁኔታዎች በዚሁ ከቀጠሉ ዝርያው ሊጠፋ ይችላል፡፡
- ከፍተኛ የሆነ የክሰል ማምረትና ግብይት ይካሄደል፡፡ ይህ ድርጊት በዚሁ ከቀጠለ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደ ክልሉ ደጋማና ወይናደጋማ አካባቢዎች የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ይሟጠጥና የሰው ልጅ ህልውንና ፈተና ውሥጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ በታሳቢ ጥብቅ ቦታው ብቻ ሳይሆን በአዋሳኝ ቀበሌዎች ያለው የተፈጥሮ ሀብት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- አዋሳኝ ቀበሌዎችና ወረዳዎች ለደን ልማትና ጥበቃ የሚሰጡት ትኩረት አናሳ በመሆኑ የተነሳ የሚከሰቱት ወንጀሎች ከእለት ወደ እለት እየበዙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ ሰደድ እሳት የሚያስነሱ፣ ደን የሚጨፈጭፉና አደን የሚያድኑ ግለሰቦች ላይ ገዳሙና አዋሳኝ ቀበሌዎች ክስ በሚመሰርቱበት ጊዜ አመራሩና የፍትህ አካላቱ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ስላልሆነ አጥፊዎች ቢከሰሱም በተደጋጋሚ በነጻ እንደሚለቀቁ ከአዋሳኝ ቀበሌ አመራሮችና ማህበረሰቦች እንዲሁም ከገዳሙ አባቶች ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

- ዘላቂ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እንዲያጎለብትና ከተፈጥሮ ሀብቱ ጥበቃ ጋር የሚስማሙ የግብርና ስራዎች እንዲጠናከሩ አዋሳኝ ቀበሌዎች ለማህበረሰቡና ለገዳሙ የሚያደርጉት አስተዳደራዊና ሙያዊ ድጋፍ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፡፡
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ያሉት አ/አደሮች ዘመናዊ የእንስሳት እርባታን ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ለእንስሳት ቁጥር ትልቅ ቦታ መስጠታቸውና ይህን አመለካከት ለመለወጥ የተደረገው ጥረት አጥጋቢ አለመሆኑ፡፡

2.7 **የቱሪዝም አቅም ጥናት**

በማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ዙሪያ የሚገኙ ኃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና የተፈጥሮ ቅርሶች በታሳቢ ማጎበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ካሉ የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲሁም ከገዳሙ ሃይማኖታዊ እሴት ጋር በማስተሳሰር ወደ ልማት ገብተው የቱሪስት መዳረሻ መሆን ቢችሉ በሚኖረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምክንያት ለክልሉም ሆነ ለአካባቢው ማጎበረሰብ ከፍተኛ የሆነ የማጎበረ ኢኮኖሚ አስተዋጾ ማበርከት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ቅርሶች ውስጥ በከፊል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-


2.7.1.የማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም

የማጎበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም አጭር ታሪክ

የማጎበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የሚገኘው በሰሜን ጎንደር ዞን መተማ ወረዳ ሲሆን ከጎንደር ወደ መተማ በሚወስደው የአስፓልት መንገድ 132 ኪሎ ሜትር ላይ ደረቅ አባይ ቀበሌ ሲደርሱ ወደ ግራ በመታጠፍ የጠጠሩን መንገድ በእግር ከሆነ አራት (4፡00) ስዓት፤ በመኪና ከሆነ ደግሞ 40 ደቂቃ ከተጓዙ በኋላ ግዝት በር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ ይደረሳል:: ከዚያም ከ45 ደቂቃ እስከ አንድ ስዓት በባዶ እግር ተጉዘው ይህን ጥንታዊና ታሪካዊውን ገዳም ያገኛሉ፡፡ ገዳሙ ማራኪ በሆነ ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ ባለውና ለዓይን በሚማርክ ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈነ ተራራማ ቦታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በኢትዮጵያ ቀደምትና ትልቅ ታሪክ ያለው ገዳም እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ፡፡

ገዳሙ የተመሰረተው በ4ኛው ክ/ዘመን በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግስት በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በአቡነ ሰላማ ከሳቱ ብርሃን ዘመን ነው፡፡ ጳጳሱም ከነገሥታቱ ጋር በመሆን በሀገሪቱ የነበረው ድርቅና ረሀብ ተወግዶ የጥጋብና የደስታ ዘመን ስለሆነ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ከአክሱም

ወደ ቋራ ሲጓዙ ቦታው ላይ ላዩ አንድ ታቹ ሦስት የሆነ የብርሃን አምድ ከሰማይ እስከ ምድር ተተክሎ አዩ። ነገሥታቱም የሚታየው የብርሃን አምድ ምስጢሩ ምንድን ነው በማለት ጳጳሱን ቢጠይቋቸው ከላይ አንድ መሆኑ የአንድነታቸው ከታች ሦስት መሆኑ የሦስትነታቸው ምስጢር ሲሆን ይኸውም የሚያስረዳው የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ነው በማለት በብርሃን አምድ ተተክሎ የነበረውን የምስጢር ትርጓሜ አስረዷቸው። የብርሃን አምድ የተተከለበት ተራራ ስር ደረሱ ጳጳሱም ይህ ቦታ መንፈስ እግዚአብሔር የሰፈነበት የተቀደሰ ቦታ ነውና እኛም ጫማችንን አውልቀን ሠራዊቱም ትጥቃቸውን ፈትተው መግባት አለብን ብለው ለነገሥታቱ ነገሯቸው። ነገሥታቱም ጫማቸውን አውልቀው የሠራዊታቸውንም ትጥቅ አስፈትተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ጫማቸውን ያወለቁበትና ትጥቃቸውን የፈቱበት ቦታ ግዝት በር ተብሎ በመከበር እስከ ዛሬ ድረስ አለ። ከግዝት በር ውስጥ ጫማ ተጫምቶ ባርኔጣ ደፍቶ ዝናር ታጥቆ ጎራዴ ታጥቆ ከበቅሎ ተቀምጦ የሚገባ የለም።



ምስል. 9 የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ግዝት በር መግቢያ

ከተተከለው የብርሃን አምድ ሲደርሱም መልሶ ተሰውራቸው እነርሱም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆኑን ለማጠየቅ ሰባት ቀን ሱባዔ ገቡ በሰባተኛው ቀንም የተሰውረው ምስጢር ተገለጸላቸው። በዚህ መነሻነትም ማንም እንግዳ ሰው እንደመጣ ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር መግባት አይችልም። ግዝት በር ውስጥ ከገባ በኋላ የቤተክርስቲያኑ ቅጥር ለመግባት ቢያንስ ለሰባት ቀናት በገዳሙ ስርዓት መሰረት መቆየት ይጠበቅበታል። ጳጳሱም ከሥላሴ ባገኙት ፈቃድ መሰረት ቦታውን ምቅዋመ ስላሴ በማለት በነገሥታቱ ሰራዊት አማካኝነት ቤተክርስቲያን ሰርተው ባርከው ታቦተ ስላሴን አስገቡበት። በተጨማሪም ለቦታው ጠባቂ መነኩሴ በመሾም ዳሩ እሳት መሀሉ ገነት ይሁን በማለት ለገዳሙ መተዳደሪያ ርስት ጉልት ሰጥተው ወደ አክሱም ከነገስታቱ ጋር ተመልሰዋል። ይህ ገዳም ከዚህ በኋላ ምቅዋመ ሥላሴ የሚለው ስያሜ ቀርቶ መካነ ሥላሴ እየተባለ ሲጠራ እንደነበርና መካነ ሠላሴ የሚለውን ስም ደግሞ ቀይረው ማኅበረ ስላሴ እንዲባል ያደረጉት አፄ ፋሲል መሆናቸውን በገዳሙ የተዘጋጀው መጽሔት ያስረዳል።

ገዳሙ ከተመሰረተ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ሰባት የበቁ ቅዱሳን አባቶች እንደነበሩ ይነገራል፤ ከነዚህም ውስጥ አንዱ ቅዱስ አሁን መታሰቢያቸውን ወይም ዝክራቸውን የካቲት 27 ቀን በየዓመቱ የሚከበርላቸው ጻድቁ አቡነ አምደ ሥላሴ ናቸው። አቡነ አምደ ሥላሴ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ሲሆኑ በገዳሙ የነበሩት በአጼ ሱስንዮስ ዘመን ነው። አጼ ሱስንዮስ የካቶሊክ ሃይማኖትን በኢትዮጵያ

ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆንና ህዝቡም በይፋ አንዲቀበል ካሰወጁ ከ18 ዓመት በኋላ በከባድ ደዌ ተያዙ፤ ከዚህ በሽታም የፈወሷቸው አቡነ አምደ ሥላሴ ናቸው። በተጨማሪም አጼ ሱስንዮስን ካሳመኑ በኋላ ሰኔ 21 ቀን 1624 ዓ.ም ደንቀዝ ላይ ተዋሕዶ (የእስክንድርያ ሃይማኖት) ይመለስ የሮም ካቶሊክ ይፍለስ ፋሲል ይንገስ ብለው አዋጅ በማስነገር የአጼ ሱስንዮስን ልጅ አቤቶ ፋሲልን በእርሳቸው አንጋሽነት(ቀቢነት) አጼ ፋሲል ተብለው በአባታቸው ዙፋን ላይ እንቀመጡ አድርገዋል።

አጼ ፋሲልም የተደረገውን ተዓምራት ሁሉ አይተው ምን ስርዓት እንስራላቸው ብለው መከሩ፤ ካህናቱ ቀጸላውን ከነካባው እንደደረበ ከቤተ-መንግስት ይግባ ብለው ስርዓት ሰሩላቸው። ንጉሱም ደጋውን የፈቀዱ እንደሆን ከፍርቃን አስከ ደንገል በር ቆላውን የፈቀዱ እንደሆን ከደንገል በር አስከ ድንድር ይውሰዱ አሏቸው። አቡነ አምደ ሥላሴ ግን ይህስ ለሰራዊትዎ ማደሪያ ይሁን ለእኔስ ከቀድሞ ነገስታት ለገዳሙ መተዳደሪያ የተሰጡኝ አርባ አራት ጉልት ደብር ቦታ ይገድሙልኝ አሏቸው። ንጉሱም በውግዘት ከ44ቱ ጉልት ደብር ውስጥ የገበታ ነጩን የብርሌ ጠጁን፣ የደም ዳኝነት፣ የነፍስ ዳኝነት የውርስ ከብት፣ የሰማንያና የይናፋ ዳኝነት እና ይህን የመሳሰለ ሁሉ ሰጥቸዎታለሁ የገዳሙም ስም ማኅበረ ሥላሴ ተብሎ ይጠራልዎ አላቸው። ይህም ከአጼ ፋሲል ጀምሮ በገዳሙ አገር ሲዳኝበት የነበረው ስርዓት እስከ 1966 ዓ.ም ሲሰራበት ቆይቶ በኢትዮጵያ በመጣው ለውጥ ምክንያት ዳኝነቱም ጉልቱም አንድ ላይ ቀርቷል።

ይህ ታላቅ ገዳም ዛሬም ቢሆን በርካታ የሃይማኖት አባቶችን(ጳጳሳትን) ያፈራ ነው። ለምሳሌ ያህል መምህር ገ/ማርያም (ብጹዕ አቡነ ዮሴፍ)፣ መምህር ሀዋዝ (ብጹዕ አቡነ ሰላማ)፣ መምህር ገ/ሥላሴ (ብጹዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ) በዚህ ገዳም በምናኔና ምንኩስና ይኖሩ የነበሩ ናቸው። ይህ ገዳም የሃይማኖት አባቶችን ብቻ ሳይሆን የሐገር መሪዎችንም ጭምር ያስተማረና ያሳደገ ነው። ይህ ይታወቅ ዘንድም ታላቁና ዝነኛው የኢትዮጵያ መሪ የነበሩት አፄ ቴዎድሮስ ተምረው ያደጉት ከዚሁ ገዳም ሲሆን መቃብራቸውም በዚሁ ቦታ ይገኛል።



***ምስል.10** በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ከሚገኙ የመስህብ ሃብቶች በከፊል*

የማኅበረ ሥላሴ ገዳም በውስጡ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙበት ከነዚህም መካከል የአፄ ቴወድሮስ መቃብር፣ አፄ ዮሐንስ 4ኛ ያበረከቱት የብራና ታምረ ማርያም፣ በአቡነ አምደ ሥላሴ

የተዘጋጀውና ገዳሙ የሚተዳደርበት ስርዓተ አበው መጽሐፍ ወዘተ ዋና ዋናዎቹን መጥቀስ ይቻላል። በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረትም ገዳሙን የሚያስተዳድሩት ሰባት ሹማምንት ይመደባሉ፤ እነርሱም መምህር፣ ገበዝ፣ መጋቢ፣ ዕቃ ቤት፣ ሊቀ ረድዕ፣ ዕጓል መጋቢ እና ሊቀ አበው ይባላሉ። እነዚህ ሹማምንት ማኅበሩን ተመካክረው ያስተዳድራሉ፤ በህርመት ነዋሪ ናቸው ሹመታቸውን ካላስወረዱም አይገድፉም።


ይህ ገዳም ከአብርሃ ወአጽብሀ ጀምሮ ከነገስታቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበረው ነገስታቱና መሳፍንቱ ለዚህ ገዳም መጽሐፍና ልዩ ልዩ ቅርሳቅርስ ያበረክቱ ነበር፤ ነገር ግን በተለያየ ጊዜ በገዳሙ ላይ ጥፋት ስለደረሰበት ቅርሶቻችን ጠፍተዋል። ከጥቃት የተረፉትንም ቢሆን በዘመኑ የነበሩ አባቶች ጠላት በመጣ ቁጥር ቅርሶችን ለማሸሸት እና ለትውልድ ለማቆየት ሲሉ ንዋየ ቅድሳቱንና ቅርሱን እንደያዙ በየዋሻው ፈልሰው ቀርተዋል። ገዳሙ በሱዳን በኩል አዋሳኝ ጠረፍ በመሆኑ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ወራሪዎች ጥቃት የተጋለጠ ስለነበር ላለፉት 1656 ዓመታት እንኳ አምስት ጊዜ ጥፋት ደርሶበታል። እነዚህም፡-

1. በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተሰርቶ የነበረውን ቤተክርስቲያን በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ዮዲት ጉዲት የተባለችው የሀገራችን ወራሪ ቤተክርስቲያኑን አቃጥላ መነኮሳቱን ገድላ ቅርሱን ዘርፋ ገዳሙን አጥፍታዋለች። ዮዲት ያቃጠለችውን ቤተክርስቲያን በአግብአ ጽዮን ተሰርቷል።
2. በአግብአ ጽዮን የተሰራው ቤተክርስቲያን ግራኝ መሐመድ ወረራ ጠፍቷል። በግራኝ መሐመድ ወረራ የጠፋው ቤተክርስቲያን በአፄ ሰርጸ-ድንግል ተሰርቷል።
3. በአፄ ሰርጸ-ድንግል የተሰራውን ቤተክርስቲያን የሱዳን ደርቡሾች አቃጥለውታል፤ መነኮሳቱንም ገድለዋቸዋል።
4. በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት ከ1600-1625 ዓ.ም ሃይማኖት በመፋለሱ ምክንያት በመነኮሳቱ ላይ ጫና በመፈጠሩ አቡነ አምደ ሥላሴን ጨምሮ አባቶች በመሰደዳቸው ገዳሙ ጠፍ ሆኖ ቆይቷል።
5. በአፄ ቴወድሮስ ዘመንም እንግሊዞች የገዳሙን ታሪካዊ ቅርሶች መዝብረው ዘርፈውታል።
6. በተፈሪ መኮንን አልጋ ወራሽነት እቴጌ ዘውዲቱ ከ1909-1922 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የተቃጠለውን ቤተክርስቲያን አሰርተው በተጨማሪም ለመነኮሳቱ የሚሆን የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ባለሁለት ክፍል በድንጋይና ኖራ አሰርተዋል። ይህ በንግስት

ዘውዲቱ የታነጸው ቤተክርስቲያንና የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ለስምንት ዓመታት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ በ1928 ዓ.ም ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ ገዳሙን በከባድ መሳሪያና በአውሮፕላን ሚያዚያ 13 ቀን አቃጥለውታል። በዚሁ ዓመተ ምሕረት (1928) ሚያዚያ 15 እና ሐምሌ 7 ቀን በድምሩ 28 መነኮሳትን ገድለዋቸዋል። ገዳሙን የደበደቡት አውሮፕላኖችም ወደ መጡበት ሲመለሱ አንደኛው ዋለንታ ሁለተኛው ማርዘነብ ከሚባሉ ከገዳሙ ቅርብ ዕርቀት ቦታዎች ላይ አውሮፕላኖቹ ወድቀዋል።

ከታሪካዊና ኃይማኖታዊ ቅርሶች በተጨማሪም በገዳሙ (ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው) ውስጥ ከ100 በላይ የዕጽዋት ዝርያዎች፣ ከ26 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት እና ከ92 በላይ የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ለመጥፋት የተቃረቡ እንደ ዲዛ፣ የእጣን ዛፍ፣ ሽመል፣ ዞቢ፣ ቋራ የመሳሉት ከእጽዋት ዝርያዎች፤ ጉሬዛ፣ የቆላ አጋዘንና ነብር የመሳሰሉ ከእንስሳት ዝርያቸው በመመናመን ላይ ያሉና በሀገራችን እንደልብ የማይገኙ የብዝሀ ሕይዎት ሃብቶችም ይገኙበታል። በመሆኑም አካባቢው በብዝሃ ህይወት ሐብት ክምችቱ ከፍተኛ የምርምር ማዕከልና የቱሪዝም መስህብ ሊሆን እንደሚችል ለማረጋገጥ ተችሏል።

የማኅበረ ሥላሴ ገዳም በአሁኑ ስዓት በዙሪያው በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ፣ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች የተረጋገጠ 19070 ሄ/ር የሚሸፍን የቆዳ ስፋት ያለው ሲሆን የአካባቢውን ብዝሀ ሕይዎትና መልከዓ ምድር በትክክል ለመመልከት የሚያግዙ በተፈጥሮ የተዘጋጁ የመመልከቻ ቦታዎች አሉት።



ምስል.11 የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

እነዚህ ቦታዎችም በገዳሙ አባቶችም የተለያየ ስያሜ ተሰጠቷቸዋል፦

- **መምህር አምባ፡** አፄ ቴዎድሮስና በርካታ አባቶች የተማሩበት እንዲሁም ገዳሙ በአሁኑ ስዓት የሚገኝበት አካባቢ ነው።

- **የከረከመችና የወርቅ አምባዎች፡** ከገዳሙ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ የሚገኙ ሲሆን በጭልጋ ወረዳ በኩል ያለውንና እስከ መምህር አምባ ድረስ የሚገኘውን አካባቢ ለመመልከት ይረዳሉ፡፡
- **ኩክቢ አምባ፡** በአካባቢው ከሚገኙት ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛ የሆነና በአለፋና ቋራ ወረዳዎችና የገዳሙን አብዛኛውን ክፍል ለመመልከት የሚረዳ ነው፡፡
- **የንጉስ አምባ(ተራራ)፡** አፄ ዮሐንስ 4ኛ ወደ መተማ ለውጊያ ሲሄዱ ገዳሙ መጥተው ያሰረፉበትና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያበረከቱበት ቦታ ሲሆን በሽመል ውኃ አካባቢ የሚገኘውን አካባቢ ለመመልከት ይረዳል፡፡
- **ጉርማስ አምባ፡** ከገዳሙ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኝ በመተማ ወረዳ የሚገኙ አዋሳኝ ቀበሌዎችንና በአምባው ዙሪያ የሚገኘውን የገዳሙን ክልል በቀላሉ ለመመልከት ይረዳል፡፡

የገዳሙ ሥርዓተ-አበው

አቡነ አምደ ሥላሴ ገዳሙን ሲመሩ ሥርዓት ሰርተዋል፤ ይኸውም፡-

1. ከገዳሙ ግዘት በር ውስጥ
- ደም አይፈስበትም፣ ጠላ አይጠመቅበትም፣ እንጀራ አይጋገርበትም
- ስብ ቅቤ እንዳይገባበት፣ ሴት እንዳይገባበት
- ሴት የቆላችው፣ የፈጨችው፣ የደቆሰችው፣ የጋገረችው ሁሉ እንዳይገባ ብለዋል፡፡
- ቅዳሜና እሁድ መግባት ክልክል ነው፤ ነገር ግን በጻድቁ በዓል፣ የሐምሌ ሥላሴና አስከሬን ለመቅበር መግባት ይፈቀዳል፡፡
2. የላመ የጣመ አይበላበትም የመነኮሳትና መናንያን ምግባቸውም ወደህ አክር ከሚባል የማሽላ ዝርያ የሚዘጋጅ መኮሬታ ነው፡፡
3. በገዳሙ ማንኛውም መናኝ መጋቢን ሳያስፈቅድ ምንም ዓይነት ስራ አይሰራም፡፡ ጥፍሩን ሲቆርጥ ጠጉሩን ሲላጭ ልብሱን ሲያጥብ መጋቢን አስፈቅዶ ነው፡፡
4. በገዳሙ የሚኖር ማንኛውም አካል የገዳሙን መተዳደሪያ ደንብ ቢያፈርስ የገዳሙ አመራሮች (ሹማምንት) ተሰብስበው “ስርዓተ አበው አንሳ” ይሉታል እርሱም “ስርዓተ አበው አንስቻለሁ” ይላል በአበው ስርዓት ለመዳኘት ፈቃደኛ ነኝ እንደ ማለት ነው፡፡ ከዚያም እንደጥፋቱ ውሳኔ ይሰጠውና ከእንጨት በተሰራች ዘውዴ በምትባል ሸንቁር

ባላት ግንድ ሁለት እግሩን አስገብቶ ይታሰራል ለብቻው በአንድ ክፍል ውስጥም እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

5. ማንኛውም መናኝ እስከ መርፌ ድረስ የግል ሃብት የለውም፡፡ ይህ ግዝት ነው፡፡

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም እንኳን ለመነኮሳቱ ለከብቶችም ቢሆን ስርዓት አላቸው፡፡ ይኸውም ጥዋት ጥጆችን ከእናታቸው ለመለየት ሲፈለግ **ወገን ወገን ወገን** እየተባለ ሲጨበጨብ ከእናታቸው ወደ ኋላ ቀርተው ለብቻቸው ይሰማራሉ እንጅ አብረው ለመሄድ ሩጫ ፍርጥጫ የለም፡፡ እንዲሁም ማታ ላይ ከእናቶቻቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ **አጎድ አጎድ አጎድ** ብሎ እረኛው ሲያጨበጭብ ከእናቶቻቸው እየተለዩ ወደ ማደሪያቸው በራሳቸው ጊዜ ይገባሉ፡፡ በተጨማሪም የነበሩበትን ቦታ ሲለቁ **ጉዞ ጉዞ ጉዞ** ሲባሉ ላም ከጥጃዋ ጋር ሳይለያዩ በአንድነት ይጓዛሉ የሚሰፍሩበት ቦታ ሲደርሱም ላም ራሱ (የላሞች ጠባቂ መናኝ/መነኩሴ) **ሰፈር ሰፈር ሰፈር** ሲሉ ሁሉም በአንድነት ይሰበሰቡና ወገን ወገን ወገን ሲባል ላሙም ወደ አንድ ወገን ጥጃውም ወደ አንድ ወገን ይሰማሩና ማታ በዚያች ሰፈር በተባሉባት ቦታ ይገናኛሉ እንጂ መምራት መጎተት የለም ይህ ሥርዓት ዛሬም አለ፡፡

የማኅበረ ሥላሴ ገዳም ከብቶች በአማራ ክልል የሚገኙ ልዩ የእንስሳት ዝርያዎች ሲሆኑ የወተት ላሞችን ዝርያ ለማሻሻልም እንደ ዝርያ ማዕከልነትም ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የሚመለከተው አካል ሁሉ የእንስሳቱን ዝርያም መጠበቅና መንከባከብ ይኖርበታል፡፡

2.7.2. በማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም ዙሪያ የሚገኙና በባህርዳር፣ ጎንደር፣ መተማ የቱሪስት መንገድ ላይ መጎብኘት የሚችሉ ዋና ዋና የባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ የቱሪዝም መስህብ ሃብቶች

የጉዛራ ቤተመንግስት

ከባህር ዳር ጎንደር በሚወስደው የአስፓልት መንገድ ስንጓዝ የጥንት ነጋዴዎች ማረፊያ ከነበረችው የእንፍራንዝ ከተማ ከመድረሳችን በፊት ወደ ቀኝ ስንመለከት ጉዛራን በጉብታው ላይ ጣናን ፊት ለፊቱ እያየ ይገኛል፡፡ ጉዛራ ማለት በግእዝ መሰባሰቢያ ቦታ፣ የጉባኤ ቦታ ማለት ነው፡፡ ከአስፓልቱ የአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለው የጉዛራ ቤተመንግሥት የጎንደር መንግሥት መስራች በሚባሉት በዐፄ ሠርጸ-ድንግል (1556-1589 ዓ.ም) አማካኝነት የተሰራ ነው፡፡

ንጉሡ በቦታው ቤተመንግሥቱን አንዲያንጹ ያደረጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች አንዳሏቸው የተለያዩ ተመራማሪዎች የዘገቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ወደ ሰሜን የሚሄደው የንግድ መስመር በዚያ የሚያልፍ መሆኑ፤ ጣና ሐይቅ ከፊት ለፊቱ የተንጣለለ መሆኑ፤ አካባቢው ደጋ መሆኑና ከወባ በሽታ ነጻ መኖኑ፤አካባቢው በእህል ምርት የታወቀ መሆኑ፤ ዋናው የወርቅ ገበያ ለነበረው ፋዞግ ቅርብ መሆኑና ሌሎችም ነበሩ።

ቤተ መንግሥቱ የጎንደርን ቤተመንግሥት መልክ ይዞ በጉብታ ላይ የታነጸ ነው። ፎቅና ምድር ቤት የነበረው ይህ ቤተመንግሥት የንጉሡ እልፍኝ፣ የፍርድ አደባባይ፣ የግብር አዳራሽ፣ ማዕድ ቤትና ሌሎችንም ክፍሎች ይዞ ነበር። ቤተመንግሥቱ ከድንጋይና ከእንጨት የተገነባ ሲሆን ከጎንደር ቤተመንግሥት የሰባ ዓመት ቅድሚያ እንዳለው ይነገራል።



ምስል12. የጉዛራ ቤተ መንግሥት ከሩቁ ሲታይ

ጎንደርና በውስጧ የሚገኙ ገጸ-በረከቶች

ጎንደር በኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ከአክሱምና ላሊበላ ቀጥሎ ትልቁ የመንግሥት ማዕከል ነበረች። በመንግሥት ማዕከልነት የተቆረቆረችው በአፄ ፋሲል (1624-1660 ዓ.ም) ነው። አፄ ፋሲል ከአባታቸው ከአፄ ሱስንዮስ ስልጣን ከተረከቡበት ከ1624 ጀምሮ ለአራት ዓመታት በደንቀዝና አዘዞ አካባቢ ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ ወደ ጎንደር በመምጣት በ1628 ዓ.ም ከተማዋን ቆርቁረዋል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አስከ ጎንደር ዘመን ማክተሚያ ፈፃሜ መንግሥት አፄ ተክለ ጊዮርጊስ (1772-1777) ድረስ የሀገሪቱ ዋና ከተማ በመሆን አገልግላለች።

ጎንደር የመንግሥት ማዕከል ብቻ ሳትሆን በጊዜው የመንፈሳዊ ትምህርት፣ የኪነ ሕንጻ ጥበብና የሌሎች የዕደ ጥበብ ውጤቶች መማሪያና መፈለቂያ ማዕከልም ነበረች። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጻሕፍት እና የአቋቋም ትምህርት ይበልጥ የተስፋፋው በየሀገሩ ያሉ ሊቃውንት በመናገሻ ከተማዋ ጎንደር በነገሥታቱ አማካይነት በመሰባሰባቸው ሲሆን ከዚያን ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ መንፈሳዊ ትምህርት በስፋት የሚሰጥባት የትምህርት ማዕከል ለመሆን ችላለች።



ምስል 13. የአፄ ፋሲል ቤተመንግስት

በአሁኑ ስዓት በዋና ከተማዋ ከ92 ያላነሱ አብያተ ክርስቲያናት ሲገኙ በአብነት ት/ቤት ረገድም የመጻሕፍት ጉባኤያት፣ የአቋቋም ምስክር፣ የቅኔ አብያተ ጉባኤያት እንዲሁም የዜማ ት/ቤቶች ይገኛሉ።

አፄ ፋሲልና ተከታዮቻቸው የሰሯቸው አብያተመንግስታትና አብያተክርስቲያናት ለከተማዋ ተደናቂነትንና ውበትን አላብሷታል። በጎንደር ከተማ ከሚገኙትና ለከተማዋ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ካሉት የቱሪስት መስህቦች መካከል የአፄ ፋሲል ግቢ፣ የአፄ ፋሲል መዋኛ፣ ራስ ግንብ፣ ደብረብርሃን ሥላሴና ቁስቋም ቤተክርስቲያንና የእቴጌ ምንትዋብ ቤተመንግስትን መጥቀስ ይቻላል።

ከእነዚህም በተጨማሪ ከአፄ ፋሲል ግቢ በሰተሰሜን አቅጣጫ 3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ወለቃ ወይም የፈላሻ መንደር እየተባለ የሚጠራውና ከአይሁዶች አመጣጥና ስራ ውጤቶቻቸው ጋር የሚያያዘው ሌላው በከተማዋ የሚገኝ የቱሪዝም የመስህብ ሃብት ነው።

የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ

የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከጥንታዊቷ ጎንደር ከተማ 118 ኪሎ ሜትር ፣ ከደባርቅ ደግሞ 18 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል። ፓርኩ ከአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በመቀጠል በ1962 ዓ.ም በሀገር ደረጃ ህጋዊ እውቅና ያገኘ ሲሆን በ1970 ዓ.ም ደግሞ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኒስኮ) በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስነት ለመመዝገብ

ችሏል። ፓርኩ ባለው ልዩ የመሬት ገጽታ (መልክዓ ምድር) እና ብርቅየ የዱር እንስሳት ምክንያት በ1970 ዓ.ም በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስነት በዩኒስኮ ቢመዘገብም በፓርኩ ላይ ይደርስ በነበረው አሉታዊ ጫና በ1978 ዓ.ም እንደገና በአደገኛ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ቅርሶች ውስጥ (in danger list) መዝግቦታል።



ምስል.14 የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ከፊል ገጽታ

ብሐራዊ ፓርኩ እካሁን በተካሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች መሰረት በውስጡ ከ1200 በላይ የእጽዋት፣ ከ22 በላይ የታላላቅ አጥቢ፣ ከ12 በላይ የታናናሽ አጥቢና ከ180 በላይ ደግሞ የአዕዋፍት ዝርያዎች መጠለያ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም 20 የእጽዋት፣ 4 የታላላቅ አጥቢዎች፣ 5 የታናናሽ አጥቢዎቻና 6 የአዕዋፋት ዝርያዎች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅየዎች ናቸው።

በአትዮጵያ ብቻ ከሚገኙት ብርቅየዎች ውስጥም ዋልያን ጨምሮ ሶስት የእጽዋት ዝርያዎች ደግሞ ከሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በስተቀር በሌላው የሀገራችን ክፍል የማይገኙ መሆናቸውን ጥናቶች ያስረዳሉ።

ድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም

ድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም ከመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ገንዳ ውኃ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በአቸራ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን ከገዳሙ ለመድረስ 55 ኪሎ ሜትሩን በመኪና ከተጓዙ በኋላ በእግር ደግሞ አንድ ስዓት መጓዝ ይጠይቃል።

ገዳሙ የተመሰረተው በግብጻዊው ጻድቅ አቡነ ቢኒያሚን ሲሆን የምስረታ ጊዜውም በአስራ አንደኛው ክ/ዘመን መጨረሻና በአስራ ሁለተኛው ክ/ዘመን መባቻ አካባቢ እንደሆነ በገዳሙ የሚገኙ አባቶች ይገልጻሉ። በተጨማሪም በገድለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንደተጻፈው አቡነ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግና አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ በዚህ ቦታ በጾምና ጸሎት ተወስነው በምነና ከቆዩ በኋላ ወደ ምድረ ከብድ ሄደዋል በማለት የቦታውን ታላቅነት ያስረዳሉ።

በነገረ መስቀል መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው ከሆነ ደግሞ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የጌታችን የመዳኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ይዘው ከግብጽ በሱዳን በኩል አድርገው ሲያልፉ በዚህ ቦታ ማረፋቸውን እና ከዚህ ተነስተው ሲሄዱ ከመስቀሉ ጋር አብሮ የመጣው አክሊለ ሶክ(በጌታ ላይ የአይሁድ ንጉስ ነህ ሲሉ አይሁዶች የደፉበት የሾህ አክሊል) ተረስቶ ቀርቶባቸዋል። ከዚያም ከተወሰነ ጉዞ በኋላ ድማህ (መሀል አናት ማለት ነው) ቀረብን ሲሏቸው ንጉሡም ተውት ፈቃዱ ስለሆነ ነው ማለታቸውንና ከዚህ ንግግር በመነሳት ቦታውን የአካበቢው ሰዎች ድሙህ ብለው እንደጠሩት ይነገራል።

ድሙህ ገዳም እጅግ ማራኪ የሆነ የመሬት አቀማመጥ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከተራራው አናት ላይ ከተወጣ በኋላ ያለው የጸጥታና እና የአርምሞ ድባብ ከሀገር በቀል እጽዋቶችና አዕዋፋት ድምጽ ጋር የፈጠረው መስተጋብር ህሊናን ወደ ማይታወቅ ዓለም ይዞ የመምጠቅ ተጽዕኖው እጅግ ከፍተኛ ነው። ገዳሙ በአሁኑ ስዓት 1050 ሄ/ር መሬት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በውስጡም ራቁታቸውን ይጓዙ በነበሩ መናኝ ከእየሩሳሌም የመጣ ነው የሚባለውን #አባ ራቁት; የዛፍ ዝርያን ጨምሮ ሌሎች ጥቁር እንጨት፣ ይገኙበታል።



ምስል 15 የድሙህ ኪዳነምሕረት ሐፊል ገጽታ

የድሙህ ኪዳነምሕረት ገዳም በአሁኑ ስዓት 22 የሚደርሱ መናኞች የሚኖሩበት ሲሆን በቦታው ላይ የተሰራ ቤተክርስቲያን የለውም። ከአሁን በፊት ቤተክርስቲያን ተሰርቶባቸው የነበሩና በደርቡሽና በጣሊያን ወረራ ጊዜ የጠፉ (የተሰውሩ) የሚካኤል፣ የመድኃኔዓለምና የኪዳነምሕረት አምባዎች እየተባሉ የሚጠሩ ሦስት ቦታዎች ይገኛሉ። በተለይም ደግሞ በኪዳነምሕረት አምባ ላይ በሚደንቅ ሁኔታ የተሰራ የድንጋይ አትሮኑስ የሚገኝ ሲሆን በዚህ አካባቢ ስውራን ባህታዊያን ለጸሎት እደሚጠቀሙበትና የቅዳሴ ድምጽም እንደሚሰማ መናንያን አባቶች ይገልጻሉ።

ገዳሙ በዕቁሪት የሚተዳደር ሲሆን የተጻፈ እንደ ማኅበረ ሥላሴ ዓይነት መተዳደሪያ ደንብ ባይኖረውም በትውፊት የተቀበሉት እና አሁን ድረስ መናንያኑ የሚተዳደሩበት ህገ ደንብ አላቸው፡፡ እነዚህም

- ✓ የጥሉላት(የፍስክ) ምግብ አይገባበትም
- ✓ አንስት አይገቡም
- ✓ በዐብይ ጾምና በፍልሰታ ጾም ጾሙ ከተጀመረ በኋላ አይገባም አይወጣም፤ ንግግርም የለም፡፡
- ✓ ቅዳሜና እሁድ መግባትና መውጣት ክልክል ነው፡፡
- ✓ እህል አይዘራበትም(ሰጢጣና ዝንጅብል ብቻ መናንያኑ በሚኖሩበት ጓሮ በመጠኑ ይፈቀዳል)
- ✓ የእርሻ ቦታና የከብት እርባታ የለውም፤ ወዘተ... የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ

የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ከጥንታዊቷ ጎንደር ከተማ 309 ኪሎ ሜትር ደቡብ ምዕራብ፣ ከገለጉ ደግሞ 25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ከ309 ኪሎ ሜትሩ ውስጥም 159 ኪ.ሜ. የሚሆነው የአስፓልት ሲሆን ቀሪው ደግሞ የጠጠር መንገድ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከባህር ዳር ተነስቶ ወደ አላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ለመድረስ ሁለት አማራጮች ያሉ ሲሆን የመጀመሪያው ከባህር ዳር በጎንደር አዘዞ ያለው ሲሆን ርቀቱም 489 ኪ.ሜ ነው፡፡ ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ከባህር ዳር በዱርበቴ ገለጉ ያለው ሲሆን ርቀቱም 350 ያህል ነው፡፡

ፓርኩ ከሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ በመቀጠል በ1998 ዓ.ም በአብክመ ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 38/1998 በፓርክነት ተመዝግቧል፡፡ ቦታው ብሔራዊ ፓርክ ሆኖ ከመመዝገቡ በፊት ባለው የተለያዩ የእጽዋትና የዱር እንስሳት ክምችት የተነሳ ጥብቅ ስፍራ መሆን እንደሚገባው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስበው እንደነበር ታሪክ ይዘክራል፡፡ ይኸውም ንጉሱ ፋሽስት ኢጣሊያ ሀገራችንን በወረረች ጊዜ ጉዳዩን ለዓለም መንግሥታት ለማስረዳት ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄደው ሲመለሱ በሱዳን በኩል ተሻግረው አሜድላ ከሚባለው አካባቢ ዲዛ በሚባል ዛፍ ውስጥ ለሰባት ቀናት ያህል ተጠልለውበት ቆይተዋል፡፡ ከዚያም በ1970ዎቹ ጀምሮ በጥብቅ ደንነት ተከልሎ እየተጠበቀ ቆይቷል፡፡



ምስል.16 የአላጥሽ ብሔራዊ ፓርክ ከፊል ገጽታ

የፓርኩ ስያሜን በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦችና ትርጓሜዎች እየተነሱ እያከራከሩ ይገኛሉ፤ አላጥሽ ማለት በአረበኛ ደረቅ ወንዝ ማለት ስለሆነ ለገጽታ ግባታው ጥሩ አይደለም ስለዚህ ይቀየርና በአፄ ቴወድሮስ ልጅ ስም አልጣሽ ይባል የሚል አንድ ወገን አለ። በሌላ በኩል ደግሞ አልጣሽ የአፄ ቴወድሮስ ልጅ ሳትሆን የእቴጌ ምንትዋብ ልጅ (የብርሃን ሰገድ የቋረኛው ኢያሱ እናት) ናት ካሉ በኋላ አላጥሽ የሚለው ስያሜም ለአልጣሽ መታሰቢያ የተሰየመ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪ የአነጋገር ዘዬ ነው ይላሉ። አልጣሽ ለሚለው ታሪካዊ መነሻም የሚከተለውን ታሪካዊ ማስረጃ ያቀርባሉ። የአድያም ሰገድ ኢያሱ ልጅ የሆኑት አፄ በካፋ ዐሥር ዓመት ነግሠው ከቆዩ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ወዲያውኑም በንጉሱ ትክ ሰው ማንገስ ግድ ነበርና እቴጌ ምንትዋብ ለመንገሥ ቢያስቡም ንጉሣዊ ዘር የለምትም ተብለው የዐሥር ዓመቱ ልጃቸው ኢያሱ ነገሠ። እቴጌይቱም በሞግዚትነት ማስተዳደር ጀመሩ። ለመንግስታቸውም ብርሃን ሰገድ ቋረኛ ኢያሱ አስብለው አሠየሙ። እቴጌ ምንትዋብ ከባለቤታቸው ከአፄ በካፋ ሞት በኋላ ኢያሱ ከሚባል ሰው በስውር እየተገናኙ ሦስት ሴት ልጆችን ወለዱ። ሦስቱ ልጆቻቸውም ወለተ እስራኤል፣ አስቴርና አልጣሽ እንደሚባሉ በጎንደር ደብረ ፀሐይ ቁስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል። ከዚያም ወለተ አስራኤል የጎጃሙን ባላባት ደጃዝማች ዮሴዴቅን አገባች። አስቴርም ራሰ ስሑልን አገባች። አልጣሽ ደግሞ የበጅሮንድ ተክለሐዋርያት ሚስት ሆነች።

ፓርኩ ያለው ለጥ ያለ የመሬት ገጽታ፣ በውስጡ የያዛቸው በመጥፋት ላይ ያሉ የብዝሐ ህይዎት ሃብቶችና በፓርኩ ዙሪያ የሚኖሩ የጉሙዝ፣ የአገውና የአማራ ብሄረሰቦች ባህል የጎብኝዎችን ቀልብ ለመሳብ የሚችሉ ገጸበረከቶቹ ናቸው። በተጨማሪም የሳህል በረሀ ሙቀትን በመከላከል በረሃማነት በሀገራችን እንዳይስፋፋ በአረንጓዴ ዘበኝነት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

እካሁን በብሔራዊ ፓርኩ በተካሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች መሰረት በውስጡ የሚኖሩ ከ130 በላይ የእጽዋት፣ ከ37 በላይ የአጥቢዎችና ከ204 በላይ ደግሞ የአዕዋፍት ዝርያዎች ተለይተዋል። ከዚህም በተጨማሪ 7 የተሳቢና ተራማጅ ዝርያዎችና 26 የዓሳ ዝርያዎች መጠለያ ሲሆን በተለይም በክልላችን ክፍሎች መገኘት የማይችሉት አንደ አንበሳና ዝሆን ያሉት ታላላቅ አጥቢዎች መኖሪያም ነው።

የአፄ ዮሐንስ ሐውልት

ይህ ሐውልት ከጎንደር ከተማ 182 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንዲሁም የመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ገንዳ ውኃ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በ20 ኪ.ሜ ርቀት ሱዳን ደንበር ላይ ከተቆረቆረችው መተማ ዮሐንስ ከተማ ክልል ውስጥ ይገኛል፡፡

እዚህ ታሪካዊ ቦታ ላይ ለሀገራቸው ዳር ድንበር መከበር ሲሉ ከድርቡሾች ጋር በነበረው ጦርነት በ1881 ዓ.ም በጀግንነት የተሰውት የንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ሐውልት ይገኛል፡፡ ካሳ ምርጫ በጥር ወር 1864 ዓ.ም (በ1872 እ.ኤ.አ.) አክሱም ላይ አፄ ዮሐንስ 4ኛ በመባል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ መተማ ላይ እከተሰውበት ድረስ ኢትዮጵያን አንድ በማድረግ ያሰተዳደሩ መሪ ነበሩ፡፡ የንጉሡን የጀግንነት ታሪክ ለመዘከርም በቆሰበትና በክብር በተሰውበት ቦታ ላይ የመታሰቢያ ሐውልት ተሰርቶላቸዋል፡፡

2.8. በታሣቢ ጥብቅ ሥፍራው በተፈጥሮ ሃብቱ ላይ የሚታዩ ተጽዕኖዎች /ስጋቶች/

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን በአርቆ አሣቢና አስተዋይ አባቶቻችን አማካይነት ለትውልድ ተጠብቆ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ቢደርስም እንኳ በአሁኑ ሰዓት የተፈጥሮ ሀብቱን ህልውና የሚፈታተኑ እርስ በርሳቸው የተሰናሰሉ ስጋቶችን ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

1. **ህገ-ወጥ የደን ጭፍጨፋ፣**

የማኅበረ ሥላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን በርካታ ለመጥፋት የተቃረቡ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ ቢሆንም ለቤት መሣሪያ፣ ለማገዶ፣ ለከሰል፣ ለጣውላና ለከብቶች ቀለብ ለመሣሰሉት አገልግሎቶች ለመጠቀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በገዳሙ ዙሪያ የሚኖሩ አንዳንድ ስግብ አርሶ አደሮች እያወደሙት ይገኛል፡፡ ይህ ችግር ደግሞ በተለይም በጭልጋ ወረዳ ሽሀርዳ ቀበሌ (እስጥንቡል ጐጥ)፣ በመተማ ወረዳ ሻሸጌ ቀበሌ (ማርዘነብና እንቡልቡል ጎጥ)፣ ሌንጫ ቀበሌ(ከሆደ ጥር ወንዝና ሽንፋ ወንዝ መገናኛ ተነስቶ ብርቂ እስከወደቀበት አካባቢ) እና አኩሻራ ቀበሌ /ከገነተ ማሪያም እስከ ሽመል ውኃ ድረስ/ ባለው ቦታ ላይ ችግሩ ግዙፍ ሆኖ ይታያል፡፡ በጥናቱ ወቅት እንደታዘብንው ለከብት ፍለጋም ይሁን ለሌላ ተግባር ወደ ገዳሙ ከሚገቡ ነዋሪዎች መካከል መጥረቢያ ሣይዝ የሚንቀሳቀስ አንድም ሰው እንደሌለ

ነው። በተለይም ደግሞ ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኘውን እንደ ሰርኪን፣ ሽመልና ቅኔ መብራት የመሣሰሉት እየተቆረጡና እየወደሙ መሆኑን ተመልክተናል።

2. ህገ-ወጥ አደን፣

በገዳሙ ውስጥ ቀደም ባሉት ጊዜያት ዝሆን፣ አንበሳና ሌሎችም ታላላቅ አጥቢዎች ይገኙበት እንደነበር ከገዳሙ አባቶች ምስክርነትና ከዱር እንሰሳቱ ቅሪት አካል ማስረጃዎች ለማወቅ ችለናል። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት በተለይ ሥጋቸው ከሚፈለጉ /ከሚባሉ/ የዱር እንሰሳት ዝርያዎች ውስጥ ጥቂት አጋዝኖች፣ ድኩላዎችና ሚዳቋዎች ብቻ ግዘት በር በምትባለው ቦታ አባቶችን ተገን አድርገው ተጠልለው ይኖራሉ። ለጥናት በሄድንበት ወቅትም ከግዘት በር ውስጥ ያሉትን እያስበረገጉ ከዚህ ክልል ሲወጡ ከአባቶች ውግዘት ነጻ ነን በማለት የዱር እንስሳቱን ለማደን ከገዳሙ በተለያየ አቅጣጫ ጥይት እየተተኮሰ ሰምተናል። ይህ ችግር በተለይም በህማማት ሰሞን አባቶች ለጾምና ጸሎት ትኩረት አድርገው ስለሚዘጉ አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች ደግሞ የጥፋት ቀስታቸውን የሚያጣጥሩበት ወቅት እንደሆነ ከነዋሪዎችና ከአባቶች ለመረዳት ችለናል።

3. ልቅ ግጦሽ፣

የአካባቢው ነዋሪዎችም ሆኑ ገዳሙ ተረፈ ምርትን ሰብስቦ ወይም ድርቆሽ በማጠራቀም እንሳሳትን የመቀለብ ልምዱ የለም። በአካባቢው ካለው የልቅ ግጦሽ ሥርዓት የተነሳም የቤት እንስሳት ወደ ደኖቹ እየገቡ የእጽዋት ቡቃያ እንዲጠፋ፣ መራቱ እንዲጠቀጠቅና እንዲጠብቅ በማድረግ የዛፍ ብቅለትን አግዷል። ይህ ሁኔታም የእጽዋቱን (በተለይም እንደ ሽመልና የጣን ዛፍ አይነቶችን) የመራባትንና እራስን የመተካት ሂደት አቋርጣል። ይህ ችግር በቋራ ወረዳ ከሚዋሰነው ኮዘራ ቀበሌ ውጪ በሌሎች አዋሣኝ 4 ቀበሌዎች በጣም ጉልቶ የሚታይ ችግር ነው።

ከአሁን በፊት በገዳሙ አባቶችና በአካባቢው ነዋሪዎች ትብብር ከላይ ከደጋው አካባቢ ከደንቢያ፣ ጣቁሳ፣ አለፋ ወረዳዎችና የጭልጋ ወረዳ ደጋ ቀበሌዎች የሚመጡ ዘላኖችን ለማቆም የተቻለ ቢሆንም በገዳሙ ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች ግን ልቅ ግጦሽን ማስቆም በሚለው አስተሳሰብ ዙሪያ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። በገዳሙ ዙሪያ ስፍረው የሚኖሩ አርሶ አደሮች የገዳሙ ይዞታ ተለይቶ ቢከለልም እንኳ ከብት በመስደድ ጥቅም እናገኛለን በማለት ልክ

እንደ እስራኤል ወታደሮችና የሀማስ ታጣቂዎች ዘወትር ከተፈጥሮ ሀብቱ ጋር ተፋጠው በመተያየት ላይ ይገኛሉ፡፡

4. ሰደድ እሣት፣

የገዳሙ አባቶች በዋናነት ለእርሻ የሚጠቀሙበትንም ይሁን ለመንገድ የሚፈልጉትን ቦታ የዛፍ ቅጠሎች እርጥበት ባለበት ወቅት ጥቅምትና ህዳር አካባቢ ቀጠጥ /Fire break/ በመስራት ጉዳት በማያመጣ መልኩ የሚያከናውኑት ቢሆንም እንኳ በገዳሙ እረኞችና በአካባቢው ነዋሪዎች የሚከናወነው የሰደድ እሣት ግን ትልቅ ችግር ሆኖ ተመልክተነዋል፡፡

በገዳሙ የተቀጠሩና የገዳሙን ከብቶች የሚጠብቁ እረኞች መኾገር ለማጥፋትና አዲስ ሣር እንዲወጣ በሚል እሣቤ ባህላዊና ጎላ ቀር በሆነ አስተሳሰብ ነባርና ሀገር በቀል ታላላቅ ዛፎች ዝርያቸውን እንዳይተኩና ባሉበት እንዲደርቁ እያደረጓቸው ይገኛል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮች ዛፎች ላይ የሚገኝን የተፈጥሮ ማር ለመቁረጥ ሲሉ በሚለኩሱት እሣት በከፍተኛ ሁኔታ የሰደድ እሣት እያስነሱ ደኑንና በውስጡ የሚገኙ ሌሎች የብዝሀ ህይወት ሃብቶችን ዝርያ እንዲጠፋ አድርገዋል፡፡



ምስል.17 የደን ሃብት ጭፍጨፋና ሳይንሱን ያልተከተለ የእጣን አመራረት

5. ሣይንሱን ያልተከተለ የእጣን አመራረት፣

በክልላችን እየጠፋ ከሚገኙና በእልቂት ስጋት ውስጥ ካሉ የተፈጥሮ ደኖች መካከል የእጣን ዛፍ አንዱ ነው፡፡ የእጣን ዛፍ ከሚገኝባቸው ጥቂት የክልሉ ቦታዎች ደግሞ የማኅበረ ሰላሴ አንድነት ገዳም አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት ከላይ ከተጠቀሱት ህገ ወጥ የደን ጭፍጨፋ፣ሰደድ እሣትና ልቅ ግጦሽ በተጨማሪ የእጣን አመራረት ሣይንስ ከሚያስተምረው መርህ ውጪ በሆነ የአመራረት እንቅስቃሴ ሀብቱ በመውደም ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህ ችግር መነሻ የሚሆኑት ደግሞ አንደኛ ከገዳሙ ጋር ውል በመያዝ የሚያመርቱ ከትግራይ ክልል የመጡ እጣን አምራቾች ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሌንጫ ቀበሌ የሚገኙ በእጣን ማምረት የተደራጁ 31 ወጣቶች ናቸው፡፡

በመስክ ለጥናት ስንቀሳቀስ እንዳየነው የማድሚያ መሣሪያቸው ምንጋፍ ሣይሆን የሾለ መጥረቢያ እንደሆነ፤ አንድን ዛፍ አንድ ቦታ ላይ ደጋግሞ ግንዱ እስኪታይ የማድማት፤ አደማሙ አቅጣጫን እየቀያየሩ ሣይሆን ከላይ እስከታች ወጥ በሆነና በተመሳሳይ አቅጣጫ መሆኑን እና አንድን ዛፍ ከ12 ጊዜ በላይ ማድማታቸውን ተመልክተናል፡፡ በዚህ ሂደት የሚቀጥል ከሆነ ማለትም ከታች አዲስ የሚተካ ሣይኖር ትልልቅ የጣን ዛፎችም ምግባቸውን እንዳይተላለፍ ተደርጐ በተከታታይ ዓመታት እየተቀጠቀጡ የሚደርቁ ከሆነ የእጣን ዛፍ በዚህ ቦታ ነበረ ብለን እንደተረት የምናወራበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም፡፡

ስለሆነም የእጣን ዛፎችን ከጥፋት ለመታደግ ልቅ ግጦሽንና ሰደድ እሳትን ማስቆም እንዲሁም ለተወሰኑ ዓመታት ከእጣን ማምረት የሚያርፉበትን ስርዓት መዘርጋትና ለምርት ሲገባም አባቶች የእጣን አመራረት ስልጠና በመውሰድ ሳይንሱን የተከተለ አመረረት በራሳቸው ማካሄድ ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

3. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ

- ሰዎች ከተፈጥሮ ሃብቱ በዘላቂነት መጠቀም የሚችሉበትንና ሰዎችና ተፈጥሮ ተጋግዘው በዘላቂነት የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ፣
- የበረሃማነት መስፋፋት ለመከላከል ያስችላል፡፡
- የአየር ንብረት ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል፡፡
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር ያስችላል
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ ፣ በተለይም በዓለም ላይ ለመጥፋት የተቃረቡ የእጽዋት ዝርያዎች እንደ ሽመል፣ ዲዛ፣ዞቢ ፣ጫሪያ እና ሰርኪን የመሳሰሉ እጽዋትንና ሌሎችን የዱር እንስሳት የዘቦታ ጥበቃ (in situ conservation) ማድረግ ያስችላል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት ፍሰት እንዲኖርና የገዳሙ ማህበረሰብና የአካባቢው ህብረተሰብ ዘላቂ የሆነ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል፣

ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ

- የገዳሙ ማህበረሰብ አባላት ከግብርና ስራ የሚያገኙት ገቢ ዘላቂነት እንዲኖረው ያስችላል፣
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው በዘላቂነት ከተጠበቀ፣ ከለማና ጥቅም ላይ ከዋለ ከማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚመረተው የእጣን ምርት ዘላቂና አስተማማኝ ስለሚሆን የገዳሙን ማህበረሰብ ገቢ ከመደጎሙ ባሻገር ለሀገርም የምንዛሬ ምንጭ ሊደግፍ ይችላል፣
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው በአግባቡ ከተጠበቀ በገዳሙና በአካበቢ አርሶ አደሮች የሚካሄድ የማር ምርት ስራ ዘላቂ ስለሚሆን የገዳሙን ማህበረሰብና የአካባቢውን ህብረተሰብ ኑሮ ይደጉማል፣
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከጉብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለገዳሙ ማህበረሰብና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣

ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- የገዳሙ ማህበረሰብ የተፈጥሮ ሃብቱን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ዘላቂ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ያስችላል።

መ/ሳይንሳዊ ጠቀሜታ

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸው ለሚደረግ ምርምር በማዕከልነት ያገለግላል። በተለይም የጎንደር ዩኒቨርስቲ በቅርብ ርቀት ስለሚገኝ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።
- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል።
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ሳይንሳዊ ምርምር ለማድረግ ያስችላል።

መ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል። በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸው ቆይተው ዘለቂታ ባለው መልክ ጥቅም እንዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል።
- የቆላማውን አካባቢ የእፅዋት ለመጠበቅ ወሳይ ናሙና በመሆን ያገለግላል።

ሠ/ የመስህብነት ጠቀሜታ

- አካባቢው ከሀይማኖታዊ ጠቀሜታው ባሻገር ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የአብነት ትምህርታቸውን የተከታተሉት ከዚሁ ገዳም ሲሆን አጽማቸው ያረፈው በአንድነት ገዳሙ ነው። አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ ማራኪ ገጽታዎች እንደ ኩክቢ፣ከርከመች፣ጉርማስ የመሳሰሉ ማራኪ ገጽታዎችን የያዘ በመሆኑ የመስህብነት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

4. **ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች**

ሀ/ ወካይነት /representativeness/

- ቦታው ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምንና በስርዓተ ምህዳር ደረጃም *Combretum-Terminalia* Woodland ስረዓተምህዳር የሚወክል ስለሆነ በማህበረሰብ በጥብቅ ስፍራነት ቢከለል የሰሜን ምዕራብ አማራ የልማት ቀጠና እና በክልላችን ቆላማው አካባቢ የአላጥሸና የባጉሳ ብሄራዊ ፓርኮች ሲኖሩ ይህን የልማት ቀጠናና ስርዓተ ምህዳር የሚወክል የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የለም ስለዚህ የቦታው መከለል በቀጠናው የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እንዲኖር ከማስቻሉም ባሻገር የጥበቃ ተሞክሮን መለዋወጥ ያስችላል።
- ከስርዓተምህዳር ውክልና በተጨማሪ በክልላችን ውስጥ ባሉ ጥብቅ ስፍራዎች ጥበቃ ያልተደረገለትን የደምበቃ ዛፍ ለመጠበቅ ወሳይ አካባቢ ነው።

ለ/ የብዛ-ህይወት ክምችት / Diversity/

- የአካባቢውን የብዝሃ-ህይወት ሃብት ስንመለከት የቆላማ አካባቢ እፅዋትን አካቶ የያዘ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ጫሪያ፣ ወንበላ፣ ሽመል፣ ዋልያ መቀር፣ ዞቢ፣ ጫብሊያ፣ ሲንሳ፣ ክርክራ፣ ደምበቃና የመሳሰሉ ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን በአካባቢው ሊጠፉ የተቃረበውን የቆላ አጋዘን መጠበቅ ከማስቻሉ በተጨማሪ ባለ ህብረ ዜማና በለህብረ ቀለማት አዕዋፍት በብዛት የሚኖሩበት ስለሆነ አካባቢውን በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት መጠበቅ ጠቀሜታው በጣም የጎላ ነው።
- አካባቢው ዙሪያውን በለሙ ቀበሌዎች የተከበበ በመሆኑ እንደ ደሴት በመሆን የብዝሃ-ህይወትንና ስርዓተ-ምህዳርን ስለሚይዝ አካባቢውን መጠበቅ የብዘሃ ህይወት ጥበቃ ማዕከል በመሆን ያገለግላል።

ሐ/ ልዩ መገለጫ / Distinctiveness/

የማህበረስላሴ አንድነት ገዳም ከሌሎች ቆላማ የብዝሃ ህይወት የጥበቃ አካባቢዎች የሚለየው ከ4ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ በአካባቢው ሰው እየኖረ ቢሆንም በገዳሙ መነኮሳት እየተጠበቀ መቆየቱ ሲሆን በገዳሙ ውስጥ ያለው ስርዓት ለመነኮሳቱ ቀርቶ የቤት እንስሳት ሳይቀር ከጠባቂዎቻቸው ጋር እንዲግባቡ ያስቻለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማህበረስላሴ አንድነት ገዳም ዙሪያውን በህዝብና የተለያዩ የእርሻ ስራዎች የሚከናወኑበት አካባቢ ሆኖ መሀል ላይ እንደ ደሴት የብዝሃህይዎት ማዕከል በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ ከዱር እንስሳት በተጨማሪ ገዳሙ የማህበረስላሴ የከብት ዝርያዎች ማዕከል በመሆኑ የእነዚህን ከብት ዝርያዎች ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል፡፡

መ/ ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ /Ecological importance/

- በታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥና በአካባቢው ያለው አባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland/ ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል
- በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ፣
- የበረሃማነት መስፋፋት ለመከላከል ያስችላል፡፡
- የአየር ንብረት ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል፡፡
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር፡ያስችላል
- የዱር እንስሳት በአይነትም ሆነ በብዛት በተፈጥሮአዊ አኗኗራቸዉ ይጠበቃሉ፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት በተፋሰሱ በተፈለገው ሁኔታ እንዲኖር ያስችላል

ሠ/ በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን /Degree of interference/

- ከባድ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር
- ሰደድ እሳትና ደን ቃጠሎ (ለካንቻ ምንጠሮና መኸርገርን ለመከላከል በሚልና በተለያዩ ምክንያቶች ሰደድ ስሳት መለኮስ)
- የእጣን ምርት ለማምረት በተገቢው መንገድና መሳሪያ አለማድማት
- የዱር እንስሳት አደን (ለሰው ምግብነት የሚውሉ የዱር እንስሳት ከመጠን በላይ መታደናቸው)

ረ/ የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ /Scientific and monitoring uses/

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈተሮአዊ አኗኗራቸዉ ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል፡፡ በተለይም የጎንደር ዩኒቨርስቲ በቅርብ ርቀት ስለሚገኝ ቦታው ህይወታዊ ላብራቶሪ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

- የዱር እንስሳት በሽታ ክስተትንና በቤትና በዱር እንስሳት መካከል ያሉ ተላላፊ የእንስሳት በሽታ ስርጭት ለማወቅ ያስችላል፡፡
- ለአካባቢ ክትትል በሚኖረው ጠቀሜታ የተፈጥሮ ሚዛን ለውጥን መለካት ያስችላል፡፡
- የዱር እፅዋት ናሙናና ተፈጥሯዊ እድገትንና በሰዎች ጣልቃ ገብነት የሚመጣዉን ለውጥ ለመለየት ይረዳል፡፡
- በቆላማ አካባቢ ለሚቋቋሙ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራዎች ለሚደረጉ ምርምሮች በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡
- በቦታው በእጣን ዛፎች ላይ ለሚደረግ ምርምር ቦታው ሊያገለግል ይችላል፡፡

ሰ/ የቦታ ስፋት /area size/

ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታው በጥብቅ ስፍራነት ተመዝግቦ በውስጡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመያዝ ቢያንስ አንድ ሽህ ሄክታር መጠበቅ ይኖርበታል የሚለውን የ IUCN መስፈርት የሚያሟላና 19070 ሄ/ር በላይ ስፋት ያለው ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ሲሆን በአገራችን ውስጥ ሱዳኖ-ጊኒ ባዮም ክልል ውስጥ ከሚገኙ 12 የአዕዋፍት ዝርያዎች ውስጥ አንድ የወፍ ዝርያ በአካባቢው ተጠልሎ እንደሚኖር በጥናቱ ወቅት የተረጋገጠ ሲሆን በተጨማሪም በአካባቢው የቆላ አጋዘንን ለመጠበቅ ከዚህ የተሻለ ቦታ የለም፡፡

ሸ/ ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ /shape/

ጥብቅ ስፍራዎች በሚቋቋሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ እንዲኖራቸው ይጠበቃል ፡፡ በመሆኑም በክልሉ እስከ አሁን ከተከለሉ ጥብቅ ስፍራዎች ከስፋታቸው አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ መጠነ ዙሪያ ያላቸውና ለጥበቃ ምቹ የሆኑ የአላጥሽ ብሄራዊ ፓርክና የማህበረሰላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ናቸው፡፡

ቀ/ በውስጡ የሚገኙ ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች /Endemicity/

ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ምንም እንኳን በውስጡ ብርቅየ ዝርያዎችን አቅፎ ባይዝም ከአዕዋፍ ዝርያዎች ውስጥ ለመጥፋት የተቃረቡት

- African white backed Vulture (EN)
- Red-footed Falcon (NT)
- White headed vulture (VU)

እንዲሁም ለዕፅዋት ዝረያዎች ውስጥ ለመጥፋት የጠቃረቡትንና ልዩ ጥበቃ የሚያሻቸውን

- ዲዛ *(Adansonia digitata)*

- ዞባ *(Dalbergia melanoxylon)*
- ሰርኪን *(Diospyros mespiliformis)*
- ጫሪያ *(Pterocarpus lucens)*
- ዋልያ መቀር (*Boswellia papyrifera*)
- ሽመል *(Oxytenanthera abyssinica አቅፎ የያዘ በመሆኑ የቦታውን መከለልና መጠበቅ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡*

ከሀ-ቀ ያሉትን መስፈርቶች ስንመለከት የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምን የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ የዳርድንበር ክለላ በሁለት የተለያዩ ጊዜያት አንድነት ገዳሙ የሚመለከታቸውን አካላትና የአካባቢውን ህብረተሰብ በመያዝ የተከናወነ በመሆኑና የጥበቃ ደረጃ ተሰጥቶት የአንድነት ገዳሙ ሊያስተዳድረው እንደሚችል የተስማማ በመሆኑ ህጋዊ እውቅና በማሰጠት ወደ ጥበቃ እንዲገባ ማስቻል ተገቢ ይሆናል፡፡

5. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ጠቀሜታና ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ማረጋገጫ መስፈርቶች ጥምረት ዝምድና

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የብዝሃህይዎት ሃብትን ለመጠበቅ በርካታ ጠቀሜታ ያለውና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ከተጠበቀና ጥቅም ላይ ከዋለ የሚሰጣቸው ጠቀሜታዎች አካባቢያዊ፤ አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም ያለው የተፈጥሮ ሽፋንና መልክዓምድራዊ አቀማመጥ የብዝሃ ህይዎትና ተፈጥሮአዊ ገፅታ ከመጠበቅ አልፎ የዓለም ሙቀትንና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የጎላ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ የተፈጥሮ ደኑ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከIUCN ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ማሟላት ከሚገባቸው መስፈርቶች ጋር ሲነፃፀር ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጠዉ ሰንጠረዥ ያለዉ የተፈጥሮ ሀብትና የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅሙን በማነፃፀር ሊጠበቅ የሚገባዉን ደረጃ ለመወሰን ያስችላል፡፡ ጥብቅ ስፍራ የመሆን መመዘኛዎችን ድምር ውጤት 87.05% ሲሆን አንድ ጥብቅ ስፍራ የታለመለትን አላማ 75% እና ከዚያ በላይ ማሳካት ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ከተገኘው የጥናት ውጤት እና ቦታው በርሃማነትን በመከላከል ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ሆኖ ቢጠበቅ

ሠንጠረዥ 5. የማህበረሰላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢጥብቅ ስፍራ ጠቀሜታና ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መመዘኛ መስፈርቶች ንፅፅር

አቅም / ጠቀሜታ	ወካይነት	ብዝሃ ህይወት	ልዩ መገለጫ	ኢኮሎጂያዊ ጠቀሚታ	በአካባቢው ላይ ያለ ጫና መጠን	የአካባቢው ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	የቦታ ስፋት/	ቅርፅ /መጠነ ዙሪያ/	ብርቅየና ድንቅየ ዝርያዎች	ደረጃ በ%
ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ዝ	77.8
የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ዝ	77.8
ማህበራዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	ከ	ከ	ከ	ዝ	77.8
ሳይንሳዊ ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	100
የመስህብነት ጠቀሜታ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ከ	ዝ	88.9
ደረጃ በ%	100	100	100	100	50	100	100	100	33.3	87.05

መፍቻ ከ፡- ከፍተኛ 1-2 ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

ዝ፡- ዝቅተኛ ከሁለት በላይ ችግሮችና የማያሟላቸዉ ነጥቦች ካሉ

አንድ የተፈጥሮ አካባቢ በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) **እንደሚመደብ ለመወሰን አካባቢው ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ማሳካት ያለበትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎችን** (Primary management objectives) **በመለየትና በማወቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሠንጠረዥ** (6) **ላይ ማየት እንደሚቻለው የተፈጥሮ አካባቢው በደረጃ** VI (protected area category VI) **መሰረት ጥብቅ ስፍራ ቢሆን በተራ ቁጥር** 3፣4 ፣6 **እና** 8 **የተቀመጡትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች የሚያሳካ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ተሰጥቶት ማቋቋም ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በአሁኑ ወቅት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመፍታት የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት እና ቦታው ህጋዊ ዕውቅና እስኪያገኝ ድረስ በአግባቡ ማስጠበቅ ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮ አካባቢው ላይ እየተፈፀሙ ያሉ ችግሮችን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እስከተቻለ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ ዓላማዎች** (Primary management objectives) **የሚያሳካ ይሆናል፡፡**

ለብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር ጥበቃ

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምን የሚወክል ሲሆን በአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር ውስጥ የሚገኙትን የዲዛ፣ ዞቢ፣ ስርኪን፣ ጫሪያና ሽመል የመሳሰሉት ዕፅዋትን እንዲሁም ሱዳኖ-ጊኒ ባዮምን መጠለያው አድረጎ የተቀመጠ አንድ የአዕዋፍ ዝረያ አቅፎ የያዘ ሲሆን በተለይም በአካባቢው ለመጥፋት የተቃረበውን የቆላ አጋዘን መጠበቅ ያስችላል፡፡ ይህን አካባቢ በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት መጠበቅ በአባሎ-ወይባ /*Combretum-Terminalia* Woodland ስርዓተ ምህዳር ውስጥ በሚገኘው የብዝሃ ህይወት ሃብት ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥር በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ ያስችላል፡፡

ሠንጠረዥ.6 ***Matrix for protected area categories and Management objectives (IUCN, 1994)***

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wildemess area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascape	Managed Resource Protected Area	
1	Scientific research	√	√	√	√	√	√	√	
2	Wilderness protection	0	0	0	0	0	0	0	
3	Preservation of species and genetic diversity	0	0	√	√	√	√	√	
4	Maintenance of environmental services	0	0	√	√	√	√	√	
5	Protection of species, natural /culture features	0	0	√	√	√	√	√	
6	Tourism and recreation	0	0	√	√	√	√	√	
7	Education	0	0	√	√	√	√	√	

No.	Management categories	IUCN protected area categories							Total (%)
		Ia	Ib	II	III	IV	V	VI	
		Strict natural reserve	Wilderness area	National Park	Natural Monument	Habitat/Species Management Area	Protected Landscape/Seascape	Managed Resource Protected Area	
8	Sustainable use of resources from natural ecosystems	0	0	0	0	0	√	√	
9	Maintenance of natural/cultural/traditional attributes	0	0	0	0	0	√	√	
	Total	1	1	6	6	6	8	8	

Note: √= can meet management objective, 0=can't meet management objective

አካባቢው የሚሰጠውን አገልግሎት /Ecosystem services/ **በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ማስቻል፤ በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳምና አካባቢው የሚነሱ ወንዞች ከገዳሙ ማህበረሰብ በተጨማሪ ለታችኛው አካባቢ በውሃ ምንጭነት የሚያገለግል ሲሆን የአካባቢውን ስርዓተ-ምህዳር ለመጠበቅ ስለሚያስችል የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም ያስችላል፡፡**

የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት በዘላቂነት መጠቀም

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ለዘመናት በገዳሙ ማህበረሰብ እየተጠበቀ የቆየ ሲሆን አሁን ግን በአካባቢው እየተካሄደ ያለው የህገወጥ እርሻ መስፋፋትና ልቅ ግጦሽ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት እየጎዳው ይገኛል፡፡ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት በዘላቂነት ለመጠቀምና ለትውልድ ለማስተላለፍ የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት በመያዝና ለአካባቢው ዘላቂ የልማት እቅድ /Management plan/ **በማዘጋጀትና አካባቢያዊ ህገደንብ በማዘጋጀት አካባቢውን በዘላቂነት ማልማትና መጠቀም ያስችላል፡፡**

የተፈጥሮ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህቦችን በመጠበቅና በማልማት ለቱሪዝም መጠቀም

ምንም እንኳን የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራዎችን ማልማትና መጠበቅ የመጀመሪያ አላማ ባይሆንም የማህበረስላሴ አንድነት ገዳም በተፈጥሮአዊና ማራኪ በሆነ የመሬት አቀማመጥ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦችን አቅፎ የያዘ በመሆኑ አካባቢውን በመጠበቅና በማልማት ለሰው

ልጆች አእምሮ ማደሻ በማድረግ ከነተፈጥሮዊ ገፅታው በማቆየት በውስጡ ያሉትን ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ሃብቶች የገዳሙን ህግ እስከተጠበቀ ድረስ በዘለቄታዊ ለቱሪዝም ልማት ጥቅም ላይ በማዋል የተፈጥሮ ሃብቱን ማስጠበቅ የሚቻልበት እድል አለ፡፡

6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- **በቂ መረጃ አለመኖር**

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራን ለማጥናት ስንቀሳቀስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚመለከታቸውን አጋር አካላትን ለማነጋገር ሞክረናል ሆኖም ግን በአንዳንድ ወረዳዎች የሚፈለገው መረጃ በበቂ ባለመገኘቱ የተቸገርን ሲሆን አንዳንድ መስሪያቤቶች የሚሰጡት መረጃ የተጋነነ መሆን በመስክ ስራው ውስጥ ካጋጠሙን ችግሮች ውስጥ ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡

- **የመስክ ደንብ ልብስና ጫማ አለመኖር**

አካባቢው ቆላማና ደን በመሆኑ ውስጥ ለውስጥ እየተሸሎከሎኩ መስራት የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር ነብሳት ጥቃት እንዳያደርሱ የመከላከያ የመስክ ልብሶች የሚያስፈልጉ ቢሆንም የደንብ ልብስ ባለመፈቀዱ አሁንም ለመስክ ስራዎች እንቅፋት በመሆን ላይ ይገኛል

- **የወረዳ ባለሙያዎች በአበል ዙሪያ ያነሱት ቅሬታ**

በመንግስት ለባለሙያዎች በተፈቀደው አበል ወረዳ ላይ የተመደቡ ባለሙያዎች ለመስራት ፈቀደኛ አለመሆን አመልድና ሌሎች NGOS በአካባቢው ሲንቀሳቀሱ የተሸለ አበል ሲከፍሉ በመቆየታቸው ከውረዳ የተመደቡ ባለሙያዎች አበሉ በቂ አይደለም በሚል ምክንያት ስራውን አብሮ ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን

7. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች

በዚህ ዝርዝር ጥናት የተዳሰሰው የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አካባቢ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ተፈጥሮዊና ስርዓተ ምህዳራዊ ወሳይነቱ ሳይቀየር ጠብቆ ለማቆየትና አግባብ ባለው መልኩ ለማልማትና ለመጠቀም ወደ ጥብቅ ስፍራነት እንዲመጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህም በክልሉ መኖር ያለበትን ወካይ ስርዓተ ምህዳር ሽፋን ከነበረበት 2 ከመቶ ከፍ እንዲልና በ5 ዓመቱ እውን ማድረግ ካለብን 7 ጥብቅ ስፍራዎች አንዱን እንድናሳካ የሚያደርግ ስራ ይሆናል። ስለዚህ ይህ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ወደ ፊት መከናውን ያለባቸው ተግባራት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

የጥናቱን ውጤት ለአጋር አካላት መላክና አስተያየት መቀበል

የዚህን ጥናት ውጤት ለቢሮው በማቅረብ ዝርዝር ውጤቱን በማሳወቅ በቢሮ ደረጃ በማጠቃለያ ሃሳቦቹ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠርና የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸዉ አካላት መላክና አስተያየት መቀበል፣

ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው በየትኛው የጥብቅ ስፍራ ደረጃ (protected area category) እንደሚመደብ መወሰን

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አካባቢው ለተፈጥሮ ጥብቅ ስፍራነት ያለውን ጠቀሜታ፣ ተስማሚውን የጥብቅ ስፍራ ደረጃ በIUCN የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (protected area category) መሰረት የትኛውን ምድብ (Protected area category I-VI) መወሰን። ምንም እንኳን በጥናት ቡድኑ Protected area category VI ሊያሟላ እንደሚችል የተረጋገጠ ቢሆንም የተፈጠሮ ሃብቱን ለማልማትና ለመጠበቅ የተሸለ አጠባበቅ ስርዓት ካለ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት አስተያየት መሰብሰብ

ሕጋዊ እውቅና ማሰጠት

በፖቴንሽያል፣ ዝርዝርና ክለላ ጥናቶች የተገኙትን ማጠቃለያዎች መነሻ በማድረግ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጠቀሜታዎች ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ለቱሪዝም ልማት ያላቸውን አስተዋፅዖ በማረጋገጥ የታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ዳር ደንበር በህግ እንዲወሰን ከፖቴንሽያል፣ ዝርዝርና ክለላ ጥናቶች የተገኙ የማጠቃለያ ሃሳቦችን የያዘ ደጋፊ ሰነድና ረቂቅ ደንብ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለውሣኔ ማቅረብና ሕጋዊ ሰውነት ማሰጠት፣

የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን መለየትና ግብዓት ማፈላለግ

ለጥበቃና ልማት በሚያመቸው የጥብቅ ስፍራዎች ደረጃ (IUCN criteria for protected area category Vl) ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው በጥብቅ ስፍራነት የሚከለልና ህጋዊ ሰውነት የሚሰጠው ከሆነ ከጽ/ቤት ግንባታ ጀምሮ ለጥበቃና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን በጥናት መለየትና አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግና አንድነት ገዳሙም የራሱን ድርሻ እንዲወጣ አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ስራ መስራት

የአጋር አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች መለየትና ማሳወቅ

በተለያዩ የጥናት፣ የጥበቃና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ማሣተፍ፣ ማሳወቅና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ዘላቂ አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ወቅታዊ ግንኙነትና ተግባራዊ እንቅስቀሴ ማድረግ፣

8. የጉዳዩ ባለቤቶችና የባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት ትንተና

ከላይ በዝርዝር የተቀመጡና ወደፊት መከናወን ያለባቸው ሌሎች አስፈላጊ ስራዎችን ለማሳካት የጉዳዩ ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በተፈለገው መጠን መወጣት ይኖረባቸዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ በዝርዝር ለተቀመጡና ወደ ፊት መስራት ላለባቸው ስራዎች ወሳኝና አጋር ናቸው ተብለው የተመረጡ ባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤቶች ተግባርና ኃለፊነት ተለይተው እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፡፡

የባህልና ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

በአዋጅ በተሠጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በቢሮው ለስራው ቀጥተኛና ተጠሪነት ያለዉ የዱር እንሰሳት ጥናት፣ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የስራ ሂደት በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ይፈጽማል

- የተፈጥሮ ሃብቱ ጉዳት እንዳይደርስበት የህጋዊ ሰውነት እስኪያገኝ ድረስ ቦታው የክትትልና ጥበቃ ስራ እንዲከናወንለት የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ያስገነዝባል፤
- ቦታው በርሃማነትን ለመከላከልና የብዝሃ ህይወት ሃብትን ለመጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ የጥብቅ ስፍራ ደረጃ አግኝቶ እንዲጠበቅ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል

- በቦታው ላይ ተጨማሪ ጥናቶች እንዲካሄዱ የማስተባበር ሚና ይኖረዋል ጥናት ያካሂዳል
- ከሰሜን ጎንደር የኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮገራም ጋር በመቀናጀት የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም የተፈጥሮ ደን ለወደፊት ስለሚደረግለት የጥበቃ ስርዓት ረቂቅ ደንብና ደጋፊ ሰነዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አጋር አካላት በማቅረብ አስተያየት ያሰባስባል
- የተፈጥሮ ደኑ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ አስፈላጊ ስራዎችን ያከናውናል
- የሚያስፈልግ የሰው ኃይልን ሰርቶ ለሲቪል ሰርቪስ ቢሮ በማቅረብ መዋቅር ማስፈቀድ
- ህጋዊ ሰውነት ካገኘ በኋላ ከማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ጋር በመተባበር የጥበቃ ስርዓቱን የሚያስተባብር ጽ/ቤት እንዲቋቋም ይሰራል፡፡

የሰሜን ጎንደር የኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮግራም

የሰሜን ጎንደር የኑሮ ማሻሻያና ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ፕሮግራም በዞኑ ውስጥ የሚከናወኑ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ስራዎች የመደገፍ የተሸለ ልምድ ቢኖረውም በማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ውስጥ በሚከተሉት ተግባራት ውስጥ እንደሚሳተፍ ይጠበቃል፡፡

- የአንድነት ገዳሙ ህጋዊ የጥበቃ ደረጃ እስኪያገኝ ድረስ ለጥበቃ ሰራተኞች ቅጥር የሚውል በጀት ለመተማ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት መመደብ
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ህጋዊ እውቅና እንዲያገኝ አውደ ጥናቶችን መደገፍ
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ህጋዊ እውቅና በሚያገኝበት ወቅት ከአሁን በፊት ለአላጥሽና ሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ እንደሚያደርገው የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ላይ ለሚደረጉ የመሰረተ-ልማት ስራዎች ድጋፍ ማድረግ
- ፕሮግራሙ በሚሳተፍባቸው ሌሎች ተግባራት ሁሉ የተፈጥሮ አካባቢው በዘላቂነት እንዲጠበቅ መደገፍ

የሰሜን ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ

- በቆላማ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው የእጠንና ሙጫ ምርት የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር እንዳይጎዳ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት ባለሃብቶች ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስገንዘብ
- በቆላማ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው የእጠንና ሙጫ ምርት የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር እንዳይጎዳ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢውን ስልጠና መስጠት

- የአንድነት ገዳሙ የግብረና ስራዎችን የሚያከናውን ቢሆንም ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት እየተደረገለት ያለው ድጋፍ ውስን በመሆኑ ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸት
- በአካባቢው ላይ ልቅ ግጦሽ ከፍተኛ ጫና እያደረሰ በመሆኑ ከደጋማ አካባቢውች ወደ ቆላማ አካቢዎች ለግጦሽ የሚደረግ እንቅስቃሴ የሚቀንስበትን ብሎም የሚቆምበትን ስርዓት መዘርጋት
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋጸ ማበርከት
- ገዳሙ በእርሻ ስራ የሚተዳደር እንደመሆኑ መጠን የገዳሙ ማህበረሰብ የዘመናዊ የግብርና ዘዴዎችን እንዲጠቀም አስፈላጊውን እገዛ እንዲያገኝ ምቹ ሁኔታ መፍጠር

የሰሜን ጎንደር ዞን አካባቢ ጥበቃ፣መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መምሪያ

- ከአንድነት ገዳሙ ውስጥ ይኖሩ የነበረና አሁን ከገዳሙ የወጡ 70 አባዎራዎች ለገዳሙ ችግር እንዳይሆኑ ትክ መሬት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት
- በቆላማ አካባቢዎች እየተካሄደ ያለው የእጠንና ሙጫ ምርት የአካባቢው ስርዓተ ምህዳር እንዳይጎዳ የኢንቨስትመንት ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት ባለሃብቶች ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማስገንዘብና አመራረቱ በአካባቢው ላይ ያለውን ተፅዕኖ መከታተል
- በአካባቢው ያለው ህገወጥ የእርሻ መስፋፋትንና ከደጋማ አካባቢዎች ወደ ቆላማ አካባቢዎች የሚደረግ ፍልሰት የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት እየጎዳ በመሆኑ የሚቆምበትን ስትራቴጅ መዘርጋት
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅዖ ማበርከት

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ

- አካባቢው ህይወታዊ ላብራቶሪ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል የአካቢውን የተፈጥሮ ሃብት፣ በአካባቢው ላይ ያሉ ተጽዕኖዎችን፣የአካባቢውን ህብረተሰብ አኗኗር፣በተፈጥሮ ኃብቱና በአካባቢው ህብረተሰብ የሚከሰቱ ግጭቶችንና የመሳሰሉ ጥናቶችን ያደርጋል፣
- ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፋቸውን ሲያዘጋጁ በአካባቢው ላይ እንዲሰሩ ያደርጋል
- ሌሎች አስፈላጊ የምርምር ስራዎችን ያከናውናል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩሉን አስተዋጸ ማበርከት

የሰሜን ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ

- የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ህጋዊ እውቅና ማግኘት እንዲችል የዞንና የወረዳ ተቋማትን ያስተባብራል
- በአካባቢ ያሉ የመስብ ሃብቶች እንዲለሙና መረጃቸው በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል

- የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት የሚደረጉ አውደጥናቶችን ያስተባብራል
- የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ለማቋቋም በሚደረጉ ጥረቶች ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ይሰራል
- የአንድነት ገዳሙ ህግ ሳይጣስ ገዳሙና የአካባቢው ማህበረሰብ ከኢኮ ቱሪዝም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት የበኩልን አስተዋፅዖ ማበርከት

የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ጽ/ቤት

- በተፈጥሮ አካባቢው የሚከሰቱ ህገወጥ ድርጊቶችን ለመከላከል ይቻል ዘንድ ለወረዳ አስተዳደርና ጸጥታ ጉዳዮች ጽ/ቤት መመሪያዎችንና የአሰራር አቅጣጫዎችን ያስተላልፋል

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አጎራባች ወረዳዎች አስተዳደር ጽ/ቤቶች

- ከአንድነት ገዳሙ ውስጥ ይኖሩ የነበረና አሁን ከገዳሙ የወጡ 70 አባዎራዎች ለገዳሙ ችግር እንዳይሆኑ ትክ መሬት የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት (የመተማ ወረዳ)
- የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አካባቢ በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠቀም አካባቢውን የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ ሰጥቶ መከለል፣ማልማትና መጠበቅ ይገባል፡፡ በመሆኑም በያሉበት ወረዳ የሚካሄደውን ተግባራትን ይመራሉ ያስተባብራል
- በወረዳው ውስጥ ያሉ አጋር አካላት ለማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ጥበቃ የበኩላቸውን እንዲያበረከረቱ ይመራል ያስተባብራል
- በአካባቢው ያለው ህገወጥ የእርሻ መስፋፋትንና ከደጋማ አካባቢዎች ወደ ቆላማ አካባቢዎች የሚደረግ ፍልሰት የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት እየጎዳ በመሆኑ የሚቆምበትን መንገድ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር እንዲከናወን ያደርጋል
- አካባቢውን በተመለከተ ቅንጂታዊ አሰራር እንዲጎለብት ተቋማትን ያስተባብራል

የማህበረ ስላሴ አንድነት ገዳም አጎራባች ወረዳዎች ግብርና ጽ/ቤቶች

